# አዲስ ዘመን

እፕድ

ሐሙስ

81ኛ ዓመት ቁጥር 251 ግንቦት 11 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# ‹‹ሕወሓት ጦርነትን እንደ አምልኮ የሚቆጥር ቡድን ነው››

- ፕሮፌሰር ሀረገወይን አሰፋ



ፎቶ ፡- በፀሐይ ንጉሤ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ጥላቻን የማያቆም፣ ሕፃናትንና አረጋውያንን ጭምር መሣሪያ አሸክሞ የሚያስጨርስ ጦርነትን እንደ አምልኮ የሚቆጥር ቡድን ነው ሲሉ ፕሮፌሰር ሀረገወይን አሰፋ ተናገሩ፡፡

ፕሮፌሰር ሀረገወይን አሰፋ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ አሸባሪው ሕወሓት ከ40ዓመታት በፊት የጀመረውን በጥላቻ የተሞላ የጦርነት ታሪክ ዛሬም እየቀጠለ ይገኛል፡፡ የሽብር ቡድኑ ይህን መጥፎ ታሪኩን እንደ እምነትና አምልኮ በመቁጠር ከበፊት የቀጠለ የጥላቻ ትርክት በማስቀጠል ሕፃናትን በ13ዓመት መሣሪያ አሸክሞ ወደ ጦር ግንባር በመላክ ጦርነት እየቀሰቀሰ ነው፡፡

ፕሮፌሰር ሀረገወይን እንደሚሉት፤ የሽብር ቡድኑ ምን እያደረገ እንዳለ አያውቅም፡፡ በፊትም ቢሆን ጦርነቱ መጀመር አልነበረበትም፡፡ የአገር መከላከያ ሠራዊት ከገበሬው ጋር ሲያጭድ ገንዘብ በማዋጣት ዓመት በዓልን ከአረጋውያን ጋር ሲያሳልፍ ነበር፡፡ በዚህ ሠራዊት ላይ ጥቃት መፈጸሙ ተገቢ አልነበረም፡፡ በዚህ ምክንያት በተጀመረው ያላባራ ጦርነት ውስጥ በርከታ ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል፡፡ ሕወሓት አሁን እያደረገ ያለውና ከዛሬ 40ዓመት በፊት ሲያደርግ የነበረው የጦርነት ታሪክ አንድ ዓይነት ነው፡፡ ይህ የሽብር ቡድኑን በጦርነት የማምለክ ባህልን የሚያሳይ ነው፡፡

ጦርነት ሲደረግ የሚጨፈርበት ቦታ ትግራይን ብቻ ነው የማውቀው ያሉት ፕሮፌሰሯ፤ ክልሉ በእናቶች ስም ጦርነት የሚሰየምበት፤ አንድ እናት ጀግና ለመባል አምስት ልጆቿን ገፍታ እንድትልክ የምትገደድበት እንደሆነም ገልጸዋል። በክልሉ ውስጥ ቡድኑ እንዳሻው


«ሕወሓት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ ፡- በፀሐይ ንጉሤ

## «የሕወሓት የጦርነት ድግስ ቀሪውን የትግራይ ወጣት ለማስጨረስ ካልሆነ በቀር የተለየ ውጤት አያመጣም»

- አትሌት ፈይሳ ሌሊሳ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ሕወሓት የሚያደርገው የጦርነት ነጋሪት ቀሪውን የትግራይ መጣት ለማስጨረስና የአገር ሰላም ለማወክ ካልሆነ በቀር የተለየ ውጤት እንደማያስገኝለት አትሌት ፈይሳ ሌሊሳ አመለከተ፡፡

አትሌት ፈይሳ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጠው አስተያየት፣ ሕወሓት ከስህተቱ የማይማርና ለትውልድ ደንታ የሌለው ስብስብ ነው፡፡ከዚህ በኋላ ለማወክ ዕድል ያገኙ ይሆናል እንጂ ለሕወሓትም ሆነ


«የሕወሓት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ ፡- በገባቦ ገብሬ

ዶክተር ፍጹም አሰፋ

## አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው በግብርናና አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨባጭ ውጤት ማስገኘቱ ተገለጸ

- ዘንድሮ በበጋ ወቅት ወደ 16ነጥብ2 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ማምረት ተችሏል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ባይተገበር ኖሮ አሁን ያለው የኑሮ ውድነት በዚህ ደረጃ ለማቆየት በጣም እንቸገር እንደነበር የፕላንና ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያውን አስመልክቶ ከዘመን መጽሔት ጋር ቆይታ ያደረጉት የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋ እንደገለጹት፤ ከዋጋ ግሽበት ጋር ተያይዞ የመጣው የኑሮ ውድነት ዜጎቻችንን በከፍተኛ ሁኔታ እያማረረና እያስጨነቀ መሆኑ እውነት ነው፡፡ ነገር ግን አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያን መተግበር የኑሮ ውድነቱን አባብሶታል ተብሎ የሚነሳው ሀሳብ ትክክል አይደለም፡፡ አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ባይተገበር ኖሮ አሁን ያለው የኑሮ ውድነት በዚህ ደረጃ ለማቆየት በጣም አስቸጋሪ ይሆን ነበር ብለዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ በግብርናው ዘርፍ እየተሠራ ያለው የበጋ መስኖ ስንዴ የሚገርም ለውጥ እየተመዘገበበት ይገኛል፡፡ ውጤቱን ገበያውን ትርጉም ባለው መንገድ እያረጋጋ ሲሄድ እያንዳንዳችን የምረዳው ይሆናል፡፡ ስንዴ ከውጭ መግዛት እንድናቆም የሚያስችልና የአገራችንን


አገር በቀል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## ‹‹የትግራይ ሕዝብ በሕወሓት የውሸት ፕሮፓጋንዳ ተታሎ ዳግም ወደ ጦርነት መግባት የለበትም››

- ኮማንደር ገብረመስቀል ወልደሚካኤል


ገጽ 2








ዜና

# ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አሸባሪው ሕወሓት ለዳግም ጦርነት የሚያደርገውን ዝግጅት እንዲያወግዝ ጥሪ ቀረበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አሸባሪው ሕወሓት ለዳግም ጦርነት የሚያደርገውን ዝግጅት በግልጽ እንዲያወግዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጥሪ አቀረበ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ከኢዜአ ጋር ባደረጉት ቆይታ፣ ኢትዮጵያ ለሰላም ያላትን ፅኑ አቋም በተግባራዊ እርምጃዎቿ እያሳየች መሆኗን ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እንዲገነዘበው የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ተናግረዋል።

በተለይም ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት አገራዊ የምክክር ኮሚሽን መቋቋሙ፣ ሰብዓዊ ዓላማ ያለው የተኩስ ማቆም መደረጉ፣ ሰብዓዊ እርዳታዎች ወደ ትግራይ ክልል እንዲገቡ በመንግሥት በኩል የተወሰዱ እርምጃዎችን በዚህ ረገድ በአብነት አንስተዋል።

ከዚህም ባሻገር ከቀድሞ የናይጄሪያ ፕሬዚዳንት ኦሊሴጎን ኦባሳንጆ፣ ከአሜሪካ ልዩ መልዕክተኞችና ሌሎችም ዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ ጋር በሰላም ጉዳይ ላይ ውይይቶች መደረጋቸውን ጠቅሰዋል።

መንግሥት አሁንም ለሰላም ያለውን አቋም የሚያሳዩ ግልፅ እርምጃዎች እየወሰደ መሆኑን ለተለያዩ የዓለም ማኅበረሰብ አካላት የማስረዳቱ ሥራ ቀጥሏል ነው ያሉት።

ሆኖም ኢትዮጵያ ለሰላም በርካታ ርቀቶችን ብትጓዝም አሸባሪው ሕወሓት ለዳግም ጦርነት እየተዘጋጀ መሆኑን አምባሳደሩ ገልጸዋል።

ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብም ይህንን የሕወሓት የዳግም ጦርነት ዝግጅትና የታጣቂ ምልመላ በትክክል ተገንዝቦ በቡድኑ ላይ ጉልህ ተፅዕኖ እንዲያሳርፍ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ብለዋል።

በመሆኑም ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አሸባሪው ሕወሓት ለጦርነት የሚያደርገውን ዝግጅትና የአስገዳጅ የታጣቂ ምልምላ እንዲያቆም በጠንካራ አቋም ሊያወግዘው ይገባል ነው ያሉት።



አምባሳደር ዲና ሙፍቲ

# ‹‹የትግራይ ሕዝብ በሕወሓት የውሸት ፕሮፓጋንዳ ተታሎ ዳግም ወደ ጦርነት መግባት የለበትም››

- ኮማንደር ገብረመስቀል ወልደሚካኤል

**ማዕረግ ገ/ሄር**

የትግራይ ሕዝብ በሕወሓት የውሸት ፕሮፓጋንዳ ተታሎ ዳግም ወደ ጦርነት መግባት የለበትም ሲሉ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) አባል ኮማንደር ገብረመስቀል ወልደሚካኤል ገለፁ።

ኮማንደር ገብረመስቀል በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስር ለሚታተመው ወጋህታ ጋዜጣ እንደተናገሩት፣ አሸባሪው ሕወሓት የትግራይን ሕዝብ በማሳሳት ሦስተኛ ጦርነት ለመክፈት እየተዘጋጀ ነው። ይህ ደግሞ ሕዝቡን የበለጠ ቀውስ ውስጥ ይከታል። የትግራይ ሕዝብ በሕወሓት የውሸት ፕሮፓጋንዳ ተታሎ ወደከፋ ችግር ውስጥ እንዳይገባ መጠንቀቅ አለበት።

ሕዝቡ ከሰላም እንጂ ከጦርነት ሊጠቀም አይችልም፤ ይህንንም በመረዳት ጥፋትን እንደገና አንቀበልም ማለት አለበት ብለዋል።



ይህ ቡድን ጦርነቱን ለማስቀጠል የሚያደርገውን ዘመቻ የትግራይ ሕዝብ በቃ ሊለው ይገባል። ይህ ኃይል የጥፋት ቡድን ነው። ሆኖም ቡድኑ ከያዘው የጥፋት መንገድ ተመልሶ የሰላምን መንገድ እንዲመርጥ እና ካልሆነ በኃይል እንዲወገድ የትግራይ ሕዝብ የተለያዩ ጫናዎችን እንዲያደርግ አሳስበዋል።

ይህ ቡድን በትግራይ ሕዝብ ላይ የተለያዩ ውድመቶችን ሲያደርስ ኖሯል። ያለፈው ግፍና መከራ ይቅር የሚባል አይደለም ብለዋል። ጦርነት አሁን ቢነሳ በአገሪቱ በተለይም በትግራይ ሕዝብ ላይ በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል። የሕወሓት መሪዎች እነሱና ቤተሰቦቻቸው በአስተማማኝ ቦታ ላይ እያሉ ሕዝቡ ለዘመናት በመከራና በስቃይ ውስጥ ለመኖር ተገዷል ብለዋል።

ሕወሓት በትግራይ ሕዝብ ላይ ሁሉንም ዓይነት ግፍ ፈጽሟል። በትግራይ ሕዝብ ሕይወት ላይ የተሳለቀ ኃይል ነው። የትግራይን ሕዝብ በማሳሳት ከሰራው ወንጀል ለማምለም በተደጋጋሚ በጦርነት አዙሪት ውስጥ መኖርን ምርጫው አድርጓል። ይህ ቡድን በትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር የነበረውን የመንግሥት ሠራተኛ በሙሉ ማለት ይቻላል በአሰቃቂ ሁኔታ ገድሏል። በዚህ ቡድን ምክንያት የትግራይ ሕዝብ አሁንም በርሃብ እየታመሰ ነው። የትግራይ ሕዝብ ከዚህ በኋላ ሳይታለል ሕወሓት ጠላታቸው መሆኑን ተረድተው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በጋራ እንዲታገሉት ጥሪ አቅርበዋል።

# «ሕዝቡን ወደ እርቅና ወደ ይቅርታ ማምጣት የሃይማኖት አባቶች ቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል»

- ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሕዝቡን ወደ እርቅና ወደ ይቅርታ ማምጣት የሃይማኖት አባቶች ቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል ሲሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ገለጹ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ የ2014ን የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባዔ በከፈቱበት ወቅት እንደገለጹት፤ የእርቅን ጥቅም በመቀበል ወደ ተሻለ ሁኔታ ለመሸጋገር ጊዜው የሚጠይቀው ተግባር በመሆኑ ሕዝቡን ወደ እርቅና ወደ ይቅርታ ማምጣት የሃይማኖት አባቶች ቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል።

ሰላም ለሃይማኖት መጠበቅና ለሕዝብ ደኅንነት መረጋገጥ ትልቅ ዋጋ እንዳለውም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ አንስተዋል።

ሰው ሁሉ ሰላምን ቢጠብቅ በሁሉ ነገር ስኬታማ መሆን እንደሚቻል የገለጹት ፓትርያርኩ በአገሪቱ በተከሰቱ ግጭቶች ሕዝቡ መንገላታቱን ተናግረዋል።

በተጨማሪም ቅዱስ ጉባዔው ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ሰላም መሥራትና መጣር ይጠበቅበታል ነው ያሉት ብፁዕነታቸው።

ሰላምንና አንድነትን ለማረጋገጥ የተከሰቱትን ችግሮች በውይይትና በድርድር ለመፍታት ሁሉም ኢትዮጵያውያን ጥረት እንዲያደርጉም ፓትርያርኩ ጥሪ አስተላልፈዋል።

# «የአማራ ክልል መንግሥት ሕግ የማስከበር ሙሉ አቅም አለው»

**- ይልቃል ከፋለ (ዶ/ር)**

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የአማራና የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ወያኔና የወያኔ ፈረሶች ናቸው ሲሉ የአማራ ክልል ርእሰ መስተዳድር ይልቃል ከፋለ (ዶ/ር) ተናገሩ።

ይልቃል ከፋለ (ዶ/ር) በወቅታዊ ጉዳዮች መግለጫ ሰጥተዋል። በመግለጫቸውም የክልሉ መንግሥት ሕግ ለማስከበር ሙሉ አቅም አለው ብለዋል።

ሕገወጦችንና ሥርዓት አልበኞችን የመቆጣጠር አቅም አለው ነው ያሉት። እየተወሰደ ያለውን የሕግ ማስከበር ሥራ ኅብረተሰቡ ከአሉባልታ ተቆጥቦ በጥንቃቄ እንዲመረምረውም አሳስበዋል።

የጦር ነጋሪት እየጎሰመ ያለውን ጠላት በመከላከያ ሠራዊት፣ በልዩ ኃይል፣ በሚሊሻና በፋኖ ሕዝባችን ደጀን አድርገን እንመክታለን ነው ያሉት።

የአማራን ሕዝብ ሰላምና ደኅንነት ለመጠበቅ እንሠራለን ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ እርስ በርሱ የተከፋፈለ ሕዝብ ለጠላት ተጋላጭ መሆኑን ተናግረዋል።

ሕዝቡ እንዲከፋፈል ዘመቻ እንደተከፈተበትም ተናግረዋል። ሕዝቡ ተከፋፍሎ እንዲዳከም እየተደረገ ነው፤ ሕዝቡ ይሄን መገንዘብ አለበት ብለዋል።

የአማራና የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ወያኔና የወያኔ ፈረሶች ናቸው፤ በግንባር አካባቢ የወያኔ ፈረስ ሆነው የሚያገለግሉትን ኃይል እየተፋለምን ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የአማራ ክልል የፀጥታ ምክር ቤት በዝርዝር አጥንቶ ክልሉን ለማዳከም የሚሠሩ ጠላቶች መኖራቸውን አረጋግጧል፤ የውስጥ ጠላቶችን ለመዋጋት የውስጥ አንድነታችንን ማጠናከር አለብን ብለዋል።

የኅብረተሰቡ በሰላም ወጥቶ የመግባት እንቅስቃሴ ችግር ውስጥ እየወደቀ መሆኑንም ተናግረዋል። ውስጡን እያዳከመና እየከፋፈለ የሚገኝ ኃይል እንዳለም አረጋግጠናል ነው ያሉት።

ሕገወጥ ተኩስ በአጭር ካልተቀጨ በስተቀር ለኅብረተሰቡ ስጋት ይሆናልም ነው ያሉት። የልማት



እንቅስቃሴዎች በሰላማዊ ሁኔታ እንዳይከናወኑ እየተደረገ መሆኑን መገንዘባቸውንም ተናግረዋል።

ሃይማኖትን ሰበብ በማድረግ እርስ በርስ በማጋደል ክልሉ የፀጥታ ስጋት ውስጥ እንዲቆይ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መገኘታቸውን አመላክተዋል። ይህም ለውጭ ጠላት ተገላጭ እንዲሆን እያደረገ መሆኑንም መገምገማቸውንም ጠቁመዋል።

በየደረጃው ያለ አመራር እየተሳተፈበት የሕግ ማስከበር ሥራው እየተከናወነ መሆኑንም አስታውቀዋል። እየተወሰደ ያለው የሕግ ማስከበር ሥራ ጅማሮው አበረታች መሆኑንም አንስተዋል።

ሕግ የማስከበሩ ሥራ የመንግሥትን ኃላፊነት የሚያረጋግጥ እና ሕዝብን የመታደግ መሆኑንም አስታውቀዋል። ወጣቶች ከመንግሥት ጋር በመሆን ለሕግ ማስከበሩ ሥራ እንዲተባበሩ ጥሪ አቅርበዋል።

ተጠርጣሪዎችን እየያዙና በውይይት ወደ መደበኛ እንቅስቃሴያቸው እንዲመለሱ የማድረግ ሥራ እንደሚሠራም አንስተዋል።

ያለ አግባብ የተያዙ ሰዎች ካሉ አጣሪ ኮሚቴው እያጣራ አፋጣኝ መፍትሔ ይሰጣል። ጥፋተኞች ግን በሕግ አግባብ ሊቀጡ ይገባል ነው ያሉት። ከክልሉ ውጪ ተይዘው ጠፉ የሚባሉት ትክክል አይደለም መስተካከል አለበትም ብለዋል። የተፈጠረ ስህተት ካለም መታረም አለበት ብለዋል።

መንግሥት እያደረገ ያለው ሕገወጦችንና ሥርዐት አልበኞችን መቆጣጠር እንጂ ሌላ ዓላማ የለውምም ብለዋል። ሕገ ወጦች ተጠያቂ መሆን አለባቸው፤ ያላጠፋ ነጻ ይሆናልም ነው ያሉት። በሕገወጦች ላይ ያለ ምኅረት እርምጃ መውሰድ አለብን፤ ይህ የመንግሥት ተግባር ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በሌላ በኩል የአማራ ክልል መንግሥት የጦር መሣሪያ አያስፈታም፤ የክልሉ መንግሥት ፋኖን የሚያዋክብ አይደለም፣ ፋኖዎችን አመስግነናል፣ ሸልመናል፣ ነገር ግን በፋኖ ስም የሚነግዱ አሉ፤ በነፃነት እና የአማራ የክብር ስም በሆነው ፋኖ እየተንጠላጠሉ ሕገ ወጥ ተግባር ለመፈጸም የሚፈልጉ አሉ፤ እኛ ሕገወጦችን እንጂ ፋኖዎችን የመንካት ዓላማ የለንም ሲሉ ተናግረዋል።

የመንግሥትን ሥራ የሚገዳደር ኃይል ሊኖር አይችልምም ብለዋል። ሕዝቡ ከፀጥታ መዋቅር ጎን እንዲሰለፍም ጥሪ አቅርበዋል። ሰላምና ደኅንነታችን በራሳችን እንገባ፣ ይህን የማድረግ አቅም አለንም ብለዋል። ማርኮ የያዘ ሰው መሣሪያውን አይነጠቅም፣ ነገር ግን ማስመዝገብ አለበትም ብለዋል።

ዓላማችን የዜጎችን ሰላምና አንድነት ጠብቀን የጋራ ጠላታችን በጋራ መጠበቅ ነው ብለዋል። ለአማራ ሕዝብ ተቆርቋሪ የሆነ ለሕዝብ ሰላምና ደኅንነት መሥራት እንደሚገባውም አንስተዋል። ሰላምን ለማስከበር በሰላማዊ መንገድ እንሠራለን፣ ከአቅም በላይ ሲሆን እርምጃ እንወስዳለንም ነው ያሉት።



ፎቶ :- በአዮብ ተፈራ

## በተለያዩ ከተሞች የክፍያ ሥርዓት ዲጂታሳይዝ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን ኢትዮ ቴሌኮም አስታወቀ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በተለያዩ ከተሞች የሚሰጡ የመንግሥትን አገልግሎቶችን የክፍያ ሥርዓት ዲጂታላይዝ ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ኢትዮ ቴሌኮም ገለፀ፡፡

ኢትዮ ቴሌኮም፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር እና ሰባት ከተሞች የሦስትዮሽ የውሃ አገልግሎት ክፍያ በቴሌብር እና በደራሽ የክፍያ መፈፀሚያ ለማድረግ ተፈራርመዋል።

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ፍሬሕይወት ታምሩ እንደገለጹት፤ የሰባት ከተሞችን የውሃ አገልግሎት በዲጂታላይዝ ክፍያ ለማስተናገድ ስምምነት ተደርጓል። ይህም የክፍያ ሥርዓትን በማዘመን ለዜጎች የተሻለ አገልግሎት መሥጠት ያስችላል፡፡

አርባምንጭ፣ ኮምቦልቻ፣ ፍኖተሰላም፣ ባህር ዳር፣ ደሴ እና እንጂባራ ከተሞች የውሃና ፍሳሽ አገልግሎቶቻቸውን እንዲሁም የሐረሪን የውሃ አቅርቦት ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመተባበር ደንበኞች ካሉበት ሆነው የውሃ አገልግሎት ክፍያቸውን መፈፀም እንዲችሉ ሥርዓት መገንባቱን ሥራ አስፈፃሚዋ ተናግረዋል፡፡

አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ በማድረግ ለደንበኞች ቀልጣፋና ምቹ ግልጋሎት ለመስጠት በትኩረት እንደሚሠሩ የገለፁት ሥራ አስፈፃሚዋ፤ የሌሎች ከተሞች መሰል የክፍያ ሥርዓት ግንባታም በሂደት ላይ እንደሆነ አስታውቀዋል።

በተፈረመው ስምምነት መሠረት ደንበኞች ካሉበት ሆነው በደራሽ የክፍያ መፈፀሚያ እና በቴሌብር የተጠቀሙትን የውሃ አገልግሎት ክፍያ ጊዜና ጉልበታቸውን ሳያባክኑ በቀላሉ መፈፀም ይችላሉም ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም የመሠረተ ልማቶች መዳረሻ ተከትሎ ለአገልግሎት የሚከፈሉ ክፍያዎችን በቀላሉ ለማከናወን የሚረዱ አዳዲስ አሠራሮችን ይዞ ብቅ እያለ ነው ያሉት ሥራ አስፈፃሚዋ፤ ከተመሠረተ አንድ ዓመት የሞላው ቴሌብር የንግድና የክፍያ ሥርዓቱን በማሳለጥ ረገድ ሰፊ ሚናውን ተወጥቷል፤ ዜጎችንም ከእንግልትና ከገንዘብ ብክነት ታድጓል ብለዋል፡፡

እንደ ፍሬሕይወት ገለፃ፤ አሁን የተዘረጋው የውሃ አገልግሎት መክፈያ ሥርዓት ዜጎችን ከእንግልትና ከጊዜ ብክነት ከመታደጉም በላይ የአገሪቱ ምርታማነት በማሳደግ ረገድ የራሱን ሚና ይጫወታል፡፡ በቀጣይ አገልግሎቱ ወደሌሎች ከተሞች እንዲሰፋ በማድረግ በመቱ፣ አርሲ ነገሌ፣ ደብረታቦር፣ አሰላ ጋምቤላና ሌሎች ከተሞች የአገልግሎት ክፍያ ሥርዓቱን ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር /ኢመደአ/ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሹመቴ ግዛው በበኩላቸው፤ ዲጂታል ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ የብዙ ነገሮች ድምር ውጤት መሆኑን በመጥቀስ፤ ዜጎች ለአገልግሎት መሰልፍ፣ በፀሐይ መመታትና መንገላታት ሳይጠበቅባቸው እነዚህን የመክፈያ ሥርዓቶች በመጠቀም የአገልግሎት ክፍያዎችን መፈፀም ይችላሉ ብለዋል፡፡

በኢመደአ የበለፀገው ደራሽ የተባለው የክፍያ ሥርዓት መፈፀሚያ ኢትዮጵያ ውስጥ ማናቸውንም ክፍያ መፈፀም የሚያስችል ነው ያሉት ዶክተር ሹመቴ፤ ከ16 በላይ ባንኮች ወደ ሥርዓቱ የገቡ ስለሆነ ዜጎች በየትኛውም ቦታና ጊዜ ለማንኛውም ዓይነት አገልግሎት ክፍያ መፈፀም እንደሚቻል ገልጸዋል።

እንደዚህ ዓይነት የክፍያ ሥርዓቶች ዜጎችን እፎይ የሚያስብሉ እና መልካም አስተዳደርንና ግልፀኝነትን የሚያሰፍኑ ናቸውም ብለዋል፡፡

# የኢትዮጵያ የሰነድ መዋዕለ ንዋዮች ገበያ ምስረታ ለማቋቋም የሚያስችል ስምምነት ተደረገ

**ሞገስ ተስፋ**




ፎቶ :- በገባቦ ገብሬ

አዲስ አበባ፡- በገንዘብ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ እና ኤፍኤስዲ አፍሪካ ገበያውን ለማቋቋም የሚስችል ስምምነት ተፈረመ። ስምምነቱ የሰነድ መዋዕለ ገበያን ለመመስረት የመጀመሪያ ምዕራፍ ነው ተብሏል።

በስምምነት ሥነሥርዓቱ ላይ የተገኙት የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ የሚቋቋመው የሰነድ መዋዕለ ንዋዮች ገበያ ለኢትዮጵያ የፋይናንስ ኢንዱስትሪ እና ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው አዲስ ዘመንን የሚያበስር ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ የሰነድ መዋዕለ ንዋዮች ገበያ ምስረታ ለማቋቋም የሚያስችል ስምምነት ትናንት በተፈራረሙበት ወቅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነው እና በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ጥምረት የሚቋቋመው የሰነድ መዋዕለ ንዋዮች ገበያ ለኢትዮጵያ የፋይናንስ ኢንዱስትሪ እና ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው አዲስ ዘመንን የሚያበስር ነው። ስምምነቱ ኢትዮጵያ የያዘችውን ራዕይ እውን ለማድረግ በሚደረጉ ጉዞዎች ውስጥ የመጀመሪያው ጽኑ እርምጃ ነው ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በፍጥነት በማደግ ላይ የሚገኝ ኢኮኖሚ፣ ከፍተኛ መጠን ያለው ካፒታልና ለኢንቨስትመንት የሚውሉ ተጨማሪ የረጅም ጊዜ የገንዘብ ምንጮችን ይፈልጋል። ስለሆነም የፋይናንስ ዘርፉን ከእውነተኛና ማህበራዊ ዘርፎች ጋር ለማስተሳሰር የካፒታል ገበያው ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

የሰነድ መዋዕለ ንዋዮች ገበያ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ለሆኑት አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የገቢ ማሰባሰቢያ መድረኮችን ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ መነደፉን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ለውጤታማነቱ ሁሉም በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ማሞ ምህረቱ በበኩላቸው እንደገለጹት፣በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በሁሉም ኢትዮጵያውያን ዘላቂ የንግድ ሥራዎችን ለመገንባት፣ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ሥራዎችን ለመፍጠርና የአገሪቱ ኢኮኖሚ የብልጽግና አካል ለመሆን የሚስችላቸውን የረጅም ጊዜ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲያገኙ የሚያስችል ስምምነት ነው።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ የመንግሥት ስትራቴጂካዊ ኢንቨስትመንት ተቋም በመሆኑ መንግሥት ስትራቴጂክ ናቸው የሚላቸውን ዘርፎች የሚመራበት ነው። ከነዚህ ዘርፎች መካከል ኢንቨስትመንትን ማካሄድ፣ የመንግሥት ሀብትን ማስተዳደር፣ የኮሜርሻል ሀብት የሚባሉ የልማት ተቋማትን በአንድ ላይ በመሰብሰብ በሙያ የተደገፈ አመራር በማስፈን ተቋማቱ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል የተቋቋመ ነው።

አቶ ማሞ ምህረቱ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ሰነድ መዋዕለ ንዋዮች ገበያ ለአቅራቢዎችና ባለሀብቶች በካፒታል ገበያው ልዩና አዲስ የሆኑ ዕድሎችን በመክፈት ብቁ የሆነ የካፒታል ድልድልን እና አጠቃቀምን የሚያበረታታ ነው። የኢትዮጵያን ታላቅ የኢኮኖሚ አጀንዳ በመደገፍ፣ የመዋዕለ ንዋይ ገበያው ለቢዝነስ፣ ለሥራ ፈጣሪዎችና በመላው ኢትዮጵያ ለሚገኙ ወጣት ባለሀብቶች በጣም አስፈላጊ የሆነው የካፒታል አቅርቦት መኖሩን ያረጋግጣል።

ኢንቨስትመንትን ወደ ኢትዮጵያ ለመሳብ በጋራ በሽርክና ከውጭ ኢንቨስተሮች ጋር በጋራ ለመስራት የተቋቋመ ነው። በመሆኑም ከተግባራቱ መካከል የሰነድ መዋዕለ ንዋዮች ለማቋቋም የሚያስችል ስምምነት መፈረሙ አስፈላጊነቱ ከፍተኛ መሆኑን ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱ የቢዝነስ አንቀሳቃሾች ሥራቸውን የተቀላጠፈ ለማድረግ እንቅፋት የሆነውን የፋይናንስ ችግር ለመቅረፍ የረጅም ጊዜ ፋይናንስ እንዲኖር ለማድረግ ሰነድ መዋዕለ ንዋዮችን ማቋቋም አስፈላጊ ነው። የቢዝነስ ተቋማት የረጅም ጊዜ ፋይናንስ ከገበያው የሚያገኙበት ዕድል ይኖራል፤ ቁጠባንም የሚያበረታታ ማዕቀፍ ይፈጠራል ሲሉ አቶ ማሞ ምህረቱ ገልጸዋል።

የኤፍኤስዲ አፍሪካ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ማርክ ናፒር ስምምነቱ የታለመለትን ግብ እንዲመታ አስፈላጊውን የቴክኒክ እና የፋይናንስ ድጋፍ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

የሰነድ መዋዕለ ንዋዮች ገበያ ምስረታው ሲጠናቀቅ በአፍሪካ 30ኛው የሰነድ መዋዕለ ንዋዮች ገበያ የሚሆን ሲሆን፣ በገበያው ባንኮች፣ ኢንሹራንሶችን ጨምሮ በትንሹ እስከ 50 ኩባንያዎች ይሳተፉበታል ተብሎ ይጠበቃል።

# «በፍርድ ቤቶች በፋይል መጥፋት ምክንያት እየተጉላላን ነው»

\- ተገልጋዮች

# «አሠራሩ ዲጂታላይዝ በመደረጉ የቆዩ ፋይሎች ካልሆኑ በስተቀር ፋይል የሚጠፋበት ሁኔታ የለም»

\- የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

ጌትነት ተስፋማርያም




አዲስ አበባ፡- በፍርድ ቤቶች በፋይል መጥፋት ምክንያት እየተጉላላን ነው ሲሉ ተገልጋዮች ቅሬታ አቅርበዋል። አሠራሩ ዲጂታላይዝ በመደረጉ ረጅም ዕድሜ ያስቆጠሩ ፋይሎች ካልሆኑ በስተቀር የፋይል መጥፋት ችግሩ መቀረፉን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አስታውቋል።

በልደታ ፍርድ ቤት አገልግሎት ፈልገው የመጡት አቶ ሰለሞን ደምሴ /ስማቸው የተቀየረ/ እና ወይዘሮ አበባ ዓለማየሁ እንደገለጹት፤ በፍርድ ቤቶች ውስጥ ያለው የፋይል መጥፋት ችግር ተገልጋዩን ለእንግልት እየዳረገ ነው። ችግሩ የፍርድ ሂደቶችን በማጓተት ቀልጣፋ አሠራር እንዳይኖር እንቅፋት ፈጥሯል።

እኔ የውርስ ጉዳይ ከጀመርኩኝ አንድ ወር ተኩል ሆኖኛል ያሉት አቶ ሰለሞን፤ ይሁንና በየጊዜው መዝገብ ቤት በተለይ ፋይልህ ጠፍቷል እየተባልኩ ጊዜዬን አባክኛለሁ። በዚህ ችግር የተነሳ በሦስት ወር ማለቅ የሚችለው ጉዳዩ ከዓመት በላይ አስቆጥሯል ብለዋል።

ይህን ዓይነት ችግር ስለገጠመኝ ለተጨማሪ ወጪና ለጊዜ ብክነት ተጋልጫለሁ የሚሉት ቅሬታ አቅራቢው፤ የችግሩን ምንጭ በመለየት በተለይ በሰነድ አያያዝና በመዝገብ ቤት ያለውን አሠራር ይበልጥ ማስተካከል ይጠበቃል ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

ሌላኛው ተገልጋይ አቶ አሽናፊ ቱፋ በበኩላቸው፤ የፍርድ ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን ጠቁመው፤ ይበልጥ ምቹ አገልግሎት ለመስጠት ግን በመዝገብ ቤት ከፋይል ጋር ተያይዞ የሚታየውን የተገልጋዮችን ወረፋ መቀነስ ይገባል ብለዋል።

በፍርድ ቤቶች ፋይል ፍለጋ የሚጠይቁ ተገልጋዮች በርካታ ናቸው። ፋይል ሲጠፋ ደግሞ የተቋሙንም አሠራር እንደሚዘገየው ይታወቃል። በመሆኑም የዳኞችን የተቀላጠፈ አሠራር ውጤታማ ለማድረግ የፋይል መጥፋት ችግሮችን በመዝገብ ቤት ማስተካከል ይገባል ሲሉ ሃሳባቸውን አቅርበዋል።

በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ችሎት ተጠሪ ዳኛ ምርምር ጥጋቡ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በፍርድ ቤቶች የፋይል መጥፋት ችግርን ለመፍታት ዲጂታል መር የሆነ አሠራር ተግባራዊ ሆኗል።

መዝገቦች በኮምፒዩተር ተመዝግበው ይቀመጣሉ፤ ኮፒያቸውም ቢሆን መዝገብ ቤት በተመሳሳይ ይገኛል። በመሆኑም ረጅም ዕድሜ ያስቆጠሩ ፋይሎችን ካልሆነ በስተቀር በቅርብ ጊዜያት የወጡ ፋይሎች አይጠፉም ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ከ1934 ዓ.ም ጀምሮ የተከፈቱ ፋይሎች አሉ ያሉት የፍርድ ቤቱ ተጠሪ ዳኛው፤ በተመሳሳይ ረጅም ዓመት ያስቆጠሩ ፋይሎችን መሠረት አድርገው የሚከፈቱ የሕግ ጉዳዮች ይኖራሉ። በዚህ ጊዜ ዓመታትን ያስቆጠሩ ፋይሎች ሲጠፉ አስፈላጊው ማጣራት ተደርጎ ሕግን መሠረት ባደረገ አካሄድ አገልግሎት የሚሰጥበት መንገድ ይመቻቻል ብለዋል።

የፍትሐብሔር ጉዳዮች አስተዳደርና ተመሳሳይ አገልግሎት የሚያቀላጥፉ አሠራሮች ተግባራዊ ከተደረጉ ጀምሮ አንድ ፋይል መቼ ተጀምሮ መቼ ማለቅ አለበት የሚለው ተቀምጦ እየተሠራበት ነው። በዚህ አሠራር 85 በመቶው በአጭር ጊዜ 10 በመቶው በመካከለኛና አምስት በመቶው ብቻ እንደጉዳዩ በረጅም ጊዜ እንዲያልቁ ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል።

አሁን ባለው አሠራር ማንኛውም መዝገብ እንደተከፈተ ወዲያው ወደሲስተም ይገባል። በዚህ አግባብ በመሠራቱ የአገልግሎት አሰጣጡም እየተሻሻለ መምጣቱን ገልጸዋል። ስለሆነም ፋይሎች የሚጠፉበት ሁኔታ የለም።

እንደ ተጠሪ ዳኛው ገለጻ፤ በ2014 ዘጠኝ ወራት ውስጥ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የተከፈቱ መዝገቦች 110 ሺህ 742 ናቸው። በዕቅድ ተይዞ ይታያል የተባለው የመዝገብ ብዛት 81 ሺህ 973 ነው። ይሁንና በዘጠኝ ወሩ ከዕቅድ በላይ 93 ሺህ 325 መዝገቦች ታይተዋል። ከተከፈቱት መዝገቦች ደግሞ 84 ነጥብ ሁለት በመቶዎቹ መዝገቦች እልባት አግኝተዋል።

## አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ትልቅ ሚና የሚጫወት ካሰብነው ጊዜ ቀድሞ እየተሳካ ያለ ሥራ ነው ብለዋል።

በአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው እንደ ግብርናው የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶታል ያሉት ሚኒስትሯ፤ በኢንዱስትሪው ዘርፍ በዚህ ዘጠኝ ወር ብቻ ከ80 በመቶ በላይ ያቀድነውን እቅድ መፈጸም ችለናል። በተመሳሳይ በውጭ ንግድ በዘጠኝ ወር ብቻ ወደ 400 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚጠጋ የውጭ ምንዛሬ አስገኝቷል። ይህ ውጤት ካለንበት ከባድ ፈተና አንጻር ቀላል የሚባል አለመሆኑን አስገንዝበዋል። የኢንዱስትሪው ዘርፍ በኮቪድ 19 ወረርሽኝና በአገር ውስጥ የገጠመን ችግር ተጨምሮበት በትልቅ ተግዳሮት ውስጥ እያለፈ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ከአመቱ እቅድ 80 በመቶውን ማሳካት መቻል ትልቅ ውጤትነው። ነገር ግን አሁን ቢሆን ብዙ ርቅት መጓዝ እንደሚጠበቅ አስገንዝበዋል።

ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር በግብርናው በተሠራው ሥራ ዘንድሮ በበጋ ወቅት ከዚህ ቀደም የማይመረትበት 504 ሺህ ሄክታር መሬት ታርሶ ወደ 16 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ማምረት ተችሏል። ይህ ባይመረት ኖሮ ሊሆን የሚችለው ምንድን ነው? ይልቁን የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው መተግበሩ በዋጋ ግሽበቱ ከዚህ እንዳይብስ የራሱን አወንታዊ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ዶክተር ፍጹም እንዳሉትም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዋጋ ግሽበቱ ዓለም አቀፋዊ ሆኗል የሚሉት ዶክተር ፍጹም፤ ያደጉ አገራት ስለ ዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት መጨነቅ ካቆሙ ብዙ ዘመን ተቆጥሮ ነበር። በኮቪድ 19 በተለይም ከራሺያና ዩክሬን ጦርነት በኋላ የዋጋ ግሽበት ሁኔታ ዓለም አቀፋዊ ሆኗል።

በስንዴ፣ በምግብዘይት፣ ማዳበሪያ፣ ማዳበሪያ በሚመረትበት ግብአት እና ነዳጅ ላይ ዓለም አቀፍ ደረጃ የዋጋ ጭማሪ መኖሩ በአገራችን ላይም የራሱ አንድምታ አለው። መንግሥት ይሄን ለመቅረፍ በፈለገው ልክ ባይሆንም ግብርና ላይ የታየው የምርትና ምርታማነት መጨመር ገበያን ለማረጋጋት የራሱ አስተዋጽኦ እንዳለው ገልጸዋል። በግጭት፣ በኮሮናና በዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ሳቢያ የዋጋ ግሽበቱ እየጨመረ እንዲሄድ ሆኗል፤ ነገር ግን እንዳይብስ ለማድረግ የአገር አቀፍ የኢኮኖሚ ማሻሻያውን መተግበራችን ከፍተኛ ሚናን መጫወት መቻሉን ገልጸዋል።

## «ሕወሓት ጦርነትን እንደ አምልኮ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የሚያደርግበት በመሆኑ ሴቶች መጠቀሚያ እንጂ እናትነታቸው እንኳን በተግባር የተገለጠበት አይደለም ይላሉ።

በተለይ ክልሉ ከድሮም ጀምሮ በጦርነት ውስጥ ያለፈ በመሆኑ ጦርነትን እንደ ትልቅ ነገር ከዚያም ባለፈ እንደ አምልኮ የመቁጠር ሁኔታ እንዳለ ጠቅሰዋል። ለልጅ ጥላቻን ማስተማር ኃላፊነት የጎደለው ተግባር ከመሆኑም በላይ ሕፃናት ላይ ጥላቻን መዝራት በሂደት የትግራይን ሕዝብ የሚጎዳ በመሆኑ ከጦርነት ታሪክና ከጥላቻ ይልቅ ፍቅር ማስተማር ከሕዝቡ እንደሚጠበቅም አስገንዝበዋል።

ፕሮፌሰር ሀረገወይን፤ ጦርነት ምንም ነገር እንደማይፈታ ከትግራይ በላይ የሚያውቅ የለም በማለት፤ ሕወሓት ጥላቻን በሕዝቡ ላይ በመርጨት ከ13ዓመት ጀምሮ በማስታጠቅ ትግራይን ወደ ኋላ እያስቀራት እንደሚገኝ፤ ለሦስተኛ ጊዜ አደርገዋለሁ የሚለውም ጦርነት ሕዝብ ለማስጨረስ እንጂ የትም እንደማያደርሰው ተናግረዋል።

«ትግራይን ነፃ እናወጣለን ነው የሚሉት። ትግራይ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ማን ኢትዮጵያዊ ሊሆን ነው? አሁንም ምን እንደሚያደርጉ ግራ ስለገባቸው ነው እንጂ ትግራይ አሁንም ያለችው በእነርሱ እጅ ነው። በአንድ በኩል ትግራይን ነፃ እናወጣለን ይላሉ በሌላ በኩል አገልግሎት ስጡን ይላሉ። አሁን ደግሞ ኤርትራን ሰብረን ወጥተን አሸንፈን ታላቋን ትግራይ እንመሠርታለን እያሉ ነው። ይህ የማይሆን ነገር ነው። ድሮስ ጎረቤት ላይኖራቸው ነበር? ይህ የመወራጨት ዓይነት ተግባር ነው።» ሲሉም ነው ፕሮፌሰር ሀረገወይን የተናገሩት።

ፕሮፌሰር ሀረገወይን አሰፋ የታዋቂዋ ጋዜጠኛ ሄርሜላ አረጋዊ እናት ሲሆኑ የሕወሓትን ሴራና ድርጊት በማጋለጥ እናትና ልጅ ግንባር ቀደም ተሳትፎ የሚያደርጉ ናቸው።

## «የሕወሓት የጦርነት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ለመሰሎቹ ኢትዮጵያን በጠብ መንጃ ኃይል መቆጣጠር ለሰማይ ያህል ሩቅ ሆኖባቸዋል፡፡

ቡድኑ እንዳሰበው ኢትዮጵያን የመበተን ዕድል የነበረው ምናልባት እንደ አሁኑ መንግሥት በሁሉም ረገድ ባልተደራጀበት ወቅትና በትጥቅና በሰው ኃይል አደረጃጀት የተሻለ ደረጃ ላይ የነበረውን ሰሜን ዕዝ ባጠቃ ማግስት ነበር የሚለው አትሌት ፈይሳ፣ በዚያን ወቅት ስለራሱ የተሳሳተ ግንዛቤ በመያዝ በለኮሰው ጦርነት በተለይ ንጹሃኑ የትግራይ ሕዝብና ወጣት ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑን ጦር ሜዳ በነበረበት ወቅት ማረጋገጡን አስገንዝቧል፡፡

እንደ አትሌቱ ማብራሪያ፣ ሕወሓት በሕዝብ ተመዝኖ የተተፋ በመሆኑ እንዳሰበው ወደ ፌዴራል መንግሥት በመመለስ ዳግም ስልጣን የመቆናጠጥ ህልሙ ቅዠት ሆኗል። ቀደም ሲል በመከላከያ ላይ በሰነዘረው ጥቃትም በኢትዮጵያ ሕዝብ ክፉኛ ተቀጥቷል። ዛሬ ላይ መንግሥት ራሱን በሁሉም ነገር ባደራጀበት ሁኔታ ላይ ኢትዮጵያን ለ3ተኛ ዙር እወጋለሁ ብሎ ከተነሳ ለበለጠ ቅጣት ወጣቱን ከማዘጋጀት ውጪ የተለየ ድል አያስገኝለትም።

ሕወሓት ምናልባት ለዘመናት ዘርፎ ያካበተውን ሀብት በመተማመን ለጥፋት ቆርጦ ከተነሳ ከምድረገጽ መሰናበቱ ግልጽ መሆኑን አትሌቱ ተናግሮ፣ እንደ ከዚህ በፊቱ አሁንም የጥፋት ድግሱን በስልጣን ዘመኑ ያልጠቀማቸውን የትግራይ ወጣቶች ለማሰለፍ ደፋ ቀና እያለ በመሆኑ የትግራይ ሕዝብ ችግሩን እንደገና ማጤን እንዳለበት መክሯል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በደም፣ በጋብቻ፣ በባህል የተሳሰረ መሆኑን የሚናገረው አትሌት ፈይሳ፣ ሆኖም አሸባሪ ኃይሉ በኢትዮጵያውያን መሃል ለዘመናት ጽንቶ የቆየውን አንድነት ለማፍረስ ለዘመናት ሲሠራ መቆየቱን ተናግሯል። በሴራ አልሳካ ሲለውም በጦርነት ፍላጎቱን ለማሳካት ቢጥርም ኪሳራ ተከናንቦ እንደተመለሰ ገልጿል።

በቀጣይም የአገሪቱን ሰላም የማይፈልጉ እና ለውይይት ዝግጁ ያልሆኑና በኃይል አገር ለማፍረስ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ላይ ጠንካራ እርምጃ በመውሰድ አገር ማስቀጠል ትልቁ የመንግሥት የቤት ሥራ መሆኑንም አትሌት ፈይሳ ጠቁሟል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጫና ፈጣሪዎችን በማስገንዘብና በማለዘብ ላይ የተመሠረተ የዲፕሎማሲ ሥራ ያስፈልጋል!

አገራችን የአገር ውስጥና የውጭ ጠላቶቿ ሉአላዊነቷን ለመዳፈር የከፈቱትን መጠነ ሰፊ ዘመቻ በህልውና ዘመቻው በአሸናፊነት ወጥታለች። ያ ሁሉ የአገር ውስጥና የውጭ ኃይሎች የተቀናጀ ርብርብ በመንግሥት አርቆ አስተዋይነትና በውድ ልጆቿ መስዋእትነት በዜሮ ተባዝቷል። በዚህም አገሪቱ የአሸባሪውን ትህነግና ደጋፊዎቹን የውጭ ኃይሎች አገር የማፈራረስ ዓላማ አምክናለች።

የህልውና ዘመቻው በጦር ሜዳ ብቻ የተገደበ አልነበረም፤ በዲፕሎማሲውም ግንባር ዘመቻ ተካሂዷል። በዲፕሎማሲ ዘመቻም ትህነግ ሀሰተኛ መረጃ እያቀነባበረ ምዕራባውያንን እና ዓለም አቀፍ ተቋማትን ጭምር ከጎኑ ቢያሰልፍም አሳፋሪ ሽንፈት ከመከናነብ አላዳነውም። ወትሮውንም የኢትዮጵያን ወደፊት መራመድ የማይፈልጉ የውጭ ኃይሎች የኢትዮጵያ ጉዳይ አበቃለት እያለ ቢጮሁም መንግሥትና ኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎች ባደረጉት የዲፕሎማሲ ርብርብ አምክነውታል።

በተለይ በበቃ ዘመቻ ዳያስፖራው በመላ ዓለም ወራትን የዘለቀ እንቅስቃሴ በማድረግ ምዕራባውያን አሸባሪውን ትህነግ በመደገፍ በኢትዮጵያ ላይ ጫና ከማድረግ እንዲቆጠቡ ሠርቷል፤ ያ ባይሆንና እንደ ምዕራባውያኑ ጫና ቢሆን አሁን ከምዕራባውያኑ ጋር እየታየ ያለው የዲፕሎማሲ ግንኙነት ባልታየም ነበር።

መንግሥት በህልውና ዘመቻው ትህነግን ከአማራና አፋር ክልሎች እንዳስወጣ ጦሩ ባለበት እንዲቆይ ማድረጉ፣ እስረኞችን መልቀቁ፣ ለአገራዊ ምክክር መድረክ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ያለበት ሁኔታም በዲፕሎማሲው መስክ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ለውጥ እንዲመጣ አስችለዋል። ትህነግና ምዕራባውያን የነዙትን ሀሰተኛ ፕሮፓጋንዳ ተከትሎ ኢትዮጵያን ለቀው የወጡ የውጭ ዜጎች መመለሳቸው፣ ሌሎች እየመጡ ያሉበት ሁኔታ፣ ከአገሮች እና ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር እየተደረጉ ያሉ ድጋፎችና ስምምነቶች እንዲሁም የሁለትዮሽ ግንኙነቶች ማንሰራራት የጀመሩት በዲፕሎማሲው መስክ የተከናወኑ ተግባሮችን ተከትሎ ነው።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ከትናንት በስቲያ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት አሁን ላይ ምዕራባውያን አገሮችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ኢትዮጵያ ላይ የሚያደርሱትን ጫና ለመቀነስና ግንኙነታቸውን ለማሻሻል አዎንታዊ ለውጦች ማሳየት መጀመራቸውን ማስታወቃቸውንም ከዚሁ አኳያ መመልከት ይቻላል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሁንም በዲፕሎማሲው መስክ መሥራት እንደሚያስፈልግ አስታውቀዋል። በተለያዩ ፍላጎቶችና የፖለቲካ አሰላለፍ ለውጦች ምክንያት እንዲሁም የዓለም ሥርዓት ተገማች ባለመሆኑ የዲፕሎማሲ ሥራው በእጅጉ ፈታኝ ሆኖ መቀጠሉ አይቀሬ መሆኑን በመጠቀስ፣ ውስጣዊ አንድነትን የማስጠበቅ እንዲሁም ሰላምን ከማረጋገጥ ጎን ጫና ፈጣሪዎችን በማስገንዘብና በማለዘብ ላይ የተመሠረተ የውጭ ግንኙነትን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

ምዕራባውያኑና ዓለም አቀፍ ተቋማት በጀርባ ተጽእኖዎችን ለመፍጠር እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ መንግሥት ይህን የውጭ ጫና ለመመከት የአሜሪካ ሴኔትና ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሁም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊዎችን ጭምር የማነጋገር ሥራ መሰራቱን አስታውቀዋል።

ይህም ጫና ፈጣሪዎችን ከማስገንዘብና ከማለዘብ አኳያ ምን ያህል እየተሠራ መሆኑን ያመለክታል። በቀጣይም አንዱ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራበት የሚገባው ይሄው ነው።

አገሪቱ ለአገራዊ ምክክር ዝግጁ ሆና እየሠራች ባለችበት በአሁኑ ወቅትም ትህነግ ከዚህ በተቃራኒው ለጦርነት እየተዘጋጀና ለእዚህም የውጭ ኃይሎች ድጋፍ እየተደረገለት እንደመሆኑ በዲፕሎማሲው መስክ መጠነ ሰፊ ሥራዎችን መሥራት የግድ ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥት ለትግራይ ሕዝብ ሰብአዊ እርዳታ እንዲገባ ሲሠራ ቆይቷል፤ አሁንም እየሠራ ነው። መድኃኒትን ጭምሮ ሰብአዊ ድጋፍ የጫኑ በርካታ ከባድ መኪኖች ድጋፉን ትግራይ አድርሰዋል፤ አሁንም ማድረሳቸውን ቀጥለዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን ትህነግ ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮኻል እንደሚባለው እርዳታ ወደ ክልሉ እንዳይገባ ኮሪደሩን የጦርነት ቀጣና አድርጎት ቆይቶ፣ እርዳታ የሚጭኑ ከባድ መኪኖች አሁንም ተመላልሰው እንዳይጭኑ እዚያው ትግራይ ውስጥ እንዲቀሩና ወታደራዊ ተግባር እንዲያከናውኑ እያደረገ ነው፤ ይህን ሁሉ እየፈጸመ ዛሬም እንደ ፊቱ የገባው ርዳታ በቂ አለመሆኑን በመግለጽ የኢትዮጵያ መንግሥትን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብና ለምዕራባውያን እየከሰሰ ነው።

ሀሰት የዘወትር ተግባሩ የሆነው አሸባሪው ትህነግ ከሚፈለገው እርዳታ 5 በመቶው ብቻ እንደገባ በመጥቀስ የትግራይ ሕዝብ በረሀብ ሊጠቃ እንደሚችል እያሟረተ ነው። ይህ ቅጥፈት አንድም የሚመከነው በዲፕሎማሲ ሥራ እንደመሆኑ ዳያስፖራው ጭምር በዚህ ላይ በትኩረት እንዲሠሩ ማድረግ ይገባል።

መንግሥት እንደ መንግሥት በዲፕሎማሲው መስክ የሚያደርገው ርብርብ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፤ ቀደም ሲል በዲፕሎማሲው መስክ በቂ ሥራ ባለመሠራቱ ሳቢያ በትህነግ እና ደጋፊዎቹ ምዕራባውያንና ዓለም አቀፍ ተቋማት ሀሰተኛ ፕሮፓጋንዳ ብዙ ዋጋ ከፍላለች። ይህ በፍጹም መደገም የለበትም።

በመላ ዓለም የሚኖረው የኢትዮጵያ ዳያስፖራ በዚያ ክፉ ወቅት አገሩን ታድጓል። በተለይ በበቃ ዘመቻ ምዕራባውያኑ ለትህነግ በመደገፍ በአገሩ ላይ እያደረሱ ያሉት ጫና እንዲያበቃ ተረባርቦ ውጤታማ መሆን ችሏል። አሁን የሚጠበቀው የዲፕሎማሲ ሥራ ደግሞ ከእስከ አሁኑም በላይ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

አንዳንድ የአሜሪካ ኮንግሬስ አባላት በኢትዮጵያ ላይ የበለጠ ጫና ሊያሳድሩ የሚችሉትን ኤች አር 6600 እና ኤስ 3199 ሕጎችን ለማጸደቅ ጥረት እያደረጉ ባሉበት በዚህ ወቅት ይህን ለመቀልበስ የኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎች ሚና ከፍተኛ ነው። ይህ ጫና ዳያስፖራውን ጭምር ከአገሩና ከወገኑ የሚያፋታ ነው እየተባለ እንደመሆኑ እዚህ ላይ በትኩረት መሥራት የግድ ይሆናል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጫና ፈጣሪዎችን በማስገንዘብና በማለዘብ የተመሠረተ የውጭ ግንኙነትን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባ ባስገነዘቡት መሠረት፣ ዲፕሎማቶችም፣ ዳያስፖራውም በተለይ በእዚህ ላይ አተኩረው የዲፕሎማሲ ሥራ በመሥራት አገርን ከምዕራባውያኑ ጫና መታደግ ይኖርባቸዋል!


አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ከኩሬ የተጣባ፤ ሐይቅ ምኑ ነው?

ዶክተር ጀኔኑስ

አንዳንድ ሰዎች ሰሞኑን መነጋገሪያ ያደረጉት ነገር ቢኖር የሕወሓት አካሄድ አስገራሚ፣ እብደት የተሞላው፣ አለማወቅ የበዛበት.... ነው እያሉ ሃሳብ ሲለዋወጡ ለመመልከት ሞክሬ ነበር። ይህ ሐሳብ ለምን መነጋገሪያ ሆነ ሲባል የትግራይን ወጣት ለስልጣኑ ሲል አገርና እና ወገን አልባ እያደረገ፤ በርሃብ አለንጋ እየገረፈ፣ የጥይት ማብረጃ እያደረገ መጓዙ ማነጋገሩ ብዙም አዲስ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን በጣም አስገራሚ የሚያደርገው ከሰማይ በታች ሕወሓትን የሚዳፈር አካል የለም፤ ሲሉ የነበሩት ወደ ትቢያ አፈር መቀየራቸው ነው። የምስራቅ አፍሪካ የኃይል ሚዛን ጠባቂ እና አስጠባቂ አድርገው ራሳቸውን የሳሉት ራሳቸውን መከላከል ተስኗቸው፤ የትግላችን መነሻ በሚሏት በደደቢት በረሃ የሕይወታቸው መጨረሻ መሆኑን ስንመለከት ነው።

ታዲያ እንደ እድል ሆኖ ከተረፉት ጥቂት የሕወሓት አመራሮችም ውስጥ አሁንም የጦርነት ነጋሪት እየጎሰሙ ኤርትራንም ኢትዮጵያንም እንሰለቅጣለን ማለታቸው ነው። ይህ ቅዠት ሕወሓት እንደሚያስበው ሊሳካ ባይችልም፤ አለው አለው ለማለት ይህን መናገራቸው አያስገርምም። ሕወሓት አሁን ቁመናው ምን ላይ ነው የሚለውን ለማወቅ በአንድ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ፓርላማ ላይ ሲናገሩ የነበረውን ማስታወስ በቂ ነው።

ይሄም ቡድኑ በአገር መከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ ይዞት የነበረው የአንድ ቡድን የበላይነት ነው። ለምሳሌ፣ ባለ አራት ኮከብ ወይንም ሙሉ ጀነራል 60 ከመቶ፣ ሌፍተናት ጀነራል 50 ከመቶ፣ ሜጀር ጀነራል 45 ከመቶ፣ ብርጋዴር ጀነራል 40 ከመቶ፣ ኮሎኔል 58 ከመቶ፣ እንዲሁም ሌተናል ኮሎኔል 66 ከመቶ፣ ሻለቃ 53 በመቶ በአንድ አካባቢ ተወላጆች የተያዘ ነበር። በጥቅሉ ከሙሉ ጄኔራል ጀምሮ እስከ ሻለቃ ድረስ በአማካይ ሲታይ 55 ከመቶ የሚሆነው ከአንድ አካባቢ ነው።

በመከላከያ ዋና መስሪያ ቤትም የሚመሩት በዋና መመሪያ እና መምሪያ ደረጃ ያሉት 80 ከመቶ ከትግራይ ክልል ነው። አመራር የሚሰጠው 80 ከመቶ ከአንድ አካባቢ ነው። ይህ ምን ማለት ደግሞ ቡድኑ የሚገዛውን ትጥቅ፣ ስልጠናው ግንኙነቱን ሁሉን በራሱ ሰንሰለት ብቻ የሚፈጽም የሚያውቀውም ራሱ ብቻ እንደነበር ነው። ቡድኑ ይሄን ሲያደርግም አቅም ያለው አመራር ከአንድ አካባቢ እንዲወጣ በማሰብ ነው። ይህ ደግሞ ለትግራይም ሆነ ለኢትዮጵያም አይጠቅምም። ምክንያቱም መከላከያ የአገር ጋሻ እንደመሆኑ በሚገባውና ባለው ህዝብ ልክ መሳተፍና አገር መጠበቅ አለበት።

ኢትዮጵያ የነበራት ዕዝ አዛዥ እና ምክትል አዛዥ መቶ በመቶ ከትግራይ ነው። ለምሳሌ፣ ሜካናይዝድ መቶ በመቶ፤ እንዲሁም በእግረኛ ክፍለጦር 80 ከመቶ ከትግራይ ነበሩ። በመከላከያ የስልጠና ተቋማትም ቢሆን 85 ከመቶ በትግራይ ልጆች የሚመሩ ነበሩ። ከለውጡ ማግስት ግን ሁሉም በሚገባው ልክ ድርሻውን መውሰድ እንዳለበት ታምኖ በሪፎርም የታገዘ ሁሉን የሚመስል የኢትዮጵያ መከላከያ ወደመገንባት ነው የተገባው።

ታዲያ በዚህ ውስጥ መረዳት የሚቻለው ነገር ቢኖር ሕወሓት አለን ብሎ ይመካበት የነበረው የአንድ ዘውግ የመከላከያ ሰራዊት አመራር ሚዛኑን በጠበቀ መንገድ መበወዙ ሳይወድ በግድ ፌጦ እንደመጋት ነበር። ቡድኑ ከአንዴም ሁለት ጊዜ ያደረገው መፍጨርጨር ከሽንፈት ያልታደገውም ይሄው ከክልል የተሻገረ ኢትዮጵያን የሚመስል መከላከያ መገንባት መቻሉ ነበር።

ከእስካሁኑ ጉዞው የምንገዘነበውም ሕወሓት ስለ እኩልነት የሚሰብክ ግን እኩልነትን የማያውቅና የማይወድ፤ ስለነፃነት እየደሰኮረ ለራሱ ነፃ ያልወጣ ድርጅት ስለመሆኑ በግልፅ መረዳት ይቻላል። ከሞያሌ እስከ ቶጎ ጫሌ፤ ከሱዳን እስከ አዲስ አበባ በተዘረጋው የእከክልኝ ልከክልህ ስብስብ ብዙ ፀረ-አገር ተግባራትን ሲያከናወኑ ነበር። በአንድ ሕወሓታዊ አስተምሮ በተጠመቀና አብዮታዊ ዴሞክራሲ ህልውናዬ ነው በሚል ጀነራል ቀጭን ትዕዛዝ አገር አምሰዋል። ታዲያ ሕወሓት ይህን ሁሉ ቅጥ ካጣ በኋላ እንዴት ሊኖር ይላል ብሎ ማሰብ ነው።

ሕወሓት አገርን መዝረፍ ብቻ ሳይሆን የአገሪቱን የዲፕሎማሲ ትስስር ከኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅም አኳያ ሳይሆን ከግለሰቦች ስብስብ ጥቅም አኳያ የተቃኘ አድርገውት ነበር። ለዚህም ማሳያ ሩቅ መሄድ አያስፈልግም። ሕወሓት በጦርነት መሸነፉን የሰሙ አሜሪካ እና አውሮፓውያን የፈጠሩትን ጫና ማስታወስ በቂ ነው። ለአብነት በአዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ 17 ጊዜ ዜጎቹ አዲስ አበባ ለቀው እንዲወጡ መግለጫና ማስፈራሪያ መሰል መረጃዎችን ማውጣቱም የሚታወስ ነው። ኤምባሲው በተደጋጋሚ የፀጥታ ስጋት መልዕክት በማውጣት ዜጎቹ በአስቸኳይ ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ሲወተውት ነበር። መንግስታትና ዓለም አቀፍ ተቋማትም ተመሳሳይ እርምጃ እንዲወስዱ ግፊት ሲያደርግ እንደነበርም ይታወሳል።

በዚህም ብቻ አላበቃም፤ ቀጣዩ ጥያቄ በኢትዮጵያ መረጋጋት እስኪሰፍን የአፍሪካ ህብረት ዋና ጽህፈት ቤት በጊዜያዊነት ወደ ሌላ አገር ይዛወር የሚል እቅድም ነበር። አሜሪካ ይህንን ለማድረግ የፈለገችው ኢትዮጵያን ገሸሽ አድርጋ የአፍሪካ ቀንድ የውጭ ፖሊሲዋን በኬንያ በኩል ለመፈጸም ስለወሰነች ሲሆን ኢትዮጵያ በአፍሪካ አገራት ዘንድ ያላትን ተደማጭነትንም ለማፈራረስ ያለመ ነበር እንደ ሃሳባቸው ባይሳካም። ዳሩ ግን የዘንድሮ የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ስብሰባ በአዲስ አበባ መካሄዱም ለሕወሓትም ለጠላቶቿችንም ራስ ምታት ነበር።

ዓለም ያልተረዳው እኛም ያላስረዳነው አንድ እውነት አለ። ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት በሕወሓት እሳቤ እና ፍልስፍና ልክ የተሰራ አለመሆኑንና በእጅጉ የገዘፈ ማንነት የተላበሰ ስለመሆኑ ማስገንዘብ አለብን። ሕወሓት ኢትዮጵያ የሚል ሰፊ እሳቤ አይገባውም። ከኩሬ የተጣባ ከሃይቅ ዝምድና የለውምና። በመሆኑም ሕወሓት ቀንደኛ ሰዎች እንጂ የሕወሓት እሳቤ አልሞተም። ኢትዮጵውያን ሕወሓት ዳግም ጦርነት ቢናፍቅ ሊገርማቸው አይገባም። የለመደው እኩል አለመሆንና ኢ- ፍትሃዊነት ነውና።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ስሁት መታጠፊያዎች... !?

አሜሪካ ካሏት አንሰላሳዮች ቀዳሚ የሆነው፤ የዝነኞቹ ሀርቫርድና የል ዩኒቨርሲቲዎች ምሩቅ፤ ትውልደ ሕንድ አሜሪካዊ፤ የአለማቀፍ ጉዳዮች ሊቅ፣ ጉምቱ ጋዜጠኛ፣ ደራሲና አንደበተ ርዕቱ ተናጋሪ ፋሪድ ዘካሪያ፤ የተወዳጁ የሲኤንኤን ቴሌቪዥን Global Public Square/GPS/ አዘጋጅ፤ የዋሽንግተን ፖስት (Washington Post) አምደኛ፤ የTIME መጽሔትን ከውጭ ሆኖ የሚደግፍ አርታኢ /editor_at large/ነው። በአለማችን ካሉ ጋዜጠኞች እንደሱ ልቅምና ጥንቅቅ ያለ ጋዜጠኛ ገጥሞኝ አያውቅም። ከአገር ውስጥ ደግሞ አፈሩን ገለባ ያድርግለትና እንደ “አዲስ ዘመኑ” ወይም የኢትዮጵያ ፕሬስ መምሪያው/ኤጀንሲው፤ ኋላ ላይ ደግሞ የ”ጦቢያው” ሙሉጌታ ሉሌ አይነት ጥልቅና ምጡቅ ጋዜጠኛ አላየሁም።

ወደተነሳሁበት ሀሳብ ስመለስ ዛሬ ለመጣጥፌ በርዕስነት ስለተዋስሁት ርዕሰ ጉዳይ ማለትም ስለ “ስሁት/የተሳሳተ መታጠፊያ፤” ወይም ውሳኔ ጦስና መዘዝ ፋሪድ በአንድ ዝግጅቱ ያነሳውን አስታውሳለሁ። “አንዳንድ ጊዜ አለምን የሚቀይሩ ሁነቶች ሊከሰቱ እንደሚችሉ አበክረን ልንገምት እንችላለን። ሌላ ጊዜ ደግሞ አጋጣሚዎች ወይም ያልተጠበቁ ሁኔታዎችና የግለሰብ ወይም የአገር መሪ የተሳሳቱ ውሳኔዎች የትውልዶችን፣ የአገራትንና የአለምን መጻኢ እድል ፈንታ እስከ ወዲያኛው ሲበይኑ እናስተውላለን፤” ይላል ፋሪድ።

ለ1ኛው የአለም ጦርነት መቀስቀስ ምክንያት የሆነውም ይሄው ስህተት ነው። የአውስትሮ _ሀንጋሪ አልጋ ወራሽ ልዑል ፍራንዝ ፈርዲናንድ የግል ሹፌር በስህተት የሰርቢያ አክራሪዎች መናኸሪያ ወደ ሆነውና አሮጌው የፍራንስ ጆሴፍ አውራ መንገድ ሲታጠፍ ከሳርያቮ ቦስንያ አክራሪ የሰርቢያ ብሔርተኛ ጋቭሪሎ ፕሪንሲፕ ጋር ፊት ለፊት ይገጣጠማል። ሹፌሩ መሳሳቱን ቢረዳም ለማረም ጊዜ አላገኘም። ጽንፈኛ ብሔርተኛው ወዲያው በታጠቀው ሽጉጥ ልዑሉንና ሚስቱን ልዕልት ሶፊን ሰኔ 28 ቀን 1914 ዓም ይገድላል። በዚህም ወደ 1ኛው የአለም ጦርነት ተገባ።

በተደጋጋሚ እንደምለው ታሪክ ራሱን ይደግማል አይደግምም የሚለው ሙግት ጉንጭ እንዳለፋ መልስ ሳያገኝ ዛሬ ድረስ የቀጠለ ቢሆንም፤ ለካርል ማርክስ ግን ታሪክ ራሱን የመድገም ጉዳይ አጠያያቂ አይደለም። ለዚህ ይመስላል፣ “ታሪክ ራሱን ሲደግም መጀመሪያ በአሳዛኝ ሁኔታ በማስከተል በአስቂኝ ሁኔታ “ ያለው።

የ2ኛው የአለም ጦርነትም በናዚው አዶልፍ ሒትለር በ1939 ዓ.ም ፖላንድን የመውረር የተሳሳተ ውሳኔ መቀስቀሱን ስንረዳ ታሪክ ለምን ራሱን አይደግም አሳምሮ ይደግማል እንጅ እንላለን። በሁለቱ ዘግናኝና አውዳሚ ጦርነቶች በአስር ሚሊዮኖቹ የሚቆጠሩ ሰዎች ሞተዋል። ቁጥራቸው ከዚህ የማይተናነስ ቆስለዋል። በቢሊየን አልያም ትሪሊየን የሚገመት ሀብትና ንብረት ወድሟል። የሰውን ልጅ ስልጣኔ ወደ ኋላ መልሰዋል።

የሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነትን ተከትሎ የሚታዩ ሁነቶችም የተሳሳተ መታጠፊያ መሆኑ ባያጠያይቅም ለመደምደም ግን ጊዜው ገና ይመስለኛል። ሆኖም 3ኛውን የአለም ጦርነት ለዛውም በኒውክሌርና በሳይበር የታገዘ ጦርነት እንዳያስነሳ ብርቱ ስጋት ደቅኗል። ጦርነቱ ላይ ላዩን ሲያዩት የራሽያና የዩክሬን ቢመስልም፤ ኔቶ፣ የተቀሩት ምዕራባውያን፣ ጃፓንና ደቡብ ኮሪያ በአንድ ጎን ራሽያ በሌላ ወገን የሚያካሂዱት የውክልና ጦርነት መሆኑ ስጋቱን ከስጋት በላይ ያደርገዋል።

የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ባለፈው አመት ለንባብ ያበቁት፤ “A Promised Land “ መጽሐፋቸው ላይ፤ “ታሪካችን የየአንዳንዳችን ውሳኔና ተግባር ድምር ውጤት ነው። ታሪክ ሁልጊዜም የእኛ ጉዳይ ነው።” ይላሉ። ይሄን ብሂል ወደ አገራችን አውድ ስናመጣው ዛሬ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ አገርና መንግስት የምንወስነው ትክክለኛም ሆነ የተሳሳተ ውሳኔ ወይም የተሳሳተ መታጠፊያ የነገ ታሪካችን አካል ነው። የተሳሳቱም ሆነ ትክክለኛ ውሳኔዎቻችን ወይም መታጠፊያዎቻችን ነገ በታሪክ ሚዛን ያስቀምጡናል። በግሌ በስሁት መታጠፊያነት ወይም ውሳኔነት የለየኋቸውን ለመማሪያነት እና በድጋሚ ላለመሳሳት በአብነት የተወሰኑትን አነሳለሁ።

ለውጡ ከባተ ካለፉት አራት አመታት ወዲህ እጅን በአፍ የሚያስጭኑ 1001 ትክክለኛ መታጠፊያዎች ተሒዶባቸዋል። ወይም ትክክለኛ ውሳኔዎች ተወስነዋል። በዚህ መጣጥፍ የማነሳው ግን በተለይ ዛሬ ከምንገኝበት ነባራዊ ሁኔታ ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ይገናኛሉ ብዬ የማምንባቸውን በተለይ የለውጥ ኃይሉንና የብልጽግናን ስሁት መታጠፊያዎች ወይም የተሳሳቱ ውሳኔዎችን ቢሆንም፤ ወደኋላ መለስ ብለን ብንፈትሽ የሕወሓት/ኢህአዴግ፣ የደርግና የቀደሙ አገዛዞችን ስሁት መታጠፊያዎችን እናገኛለን። እነዚህ የተሳሳቱ ውሳኔዎች ዛሬ ለምንገኝበት አጣብቂኝ በመዳረግ ረገድ አስተዋጾ ቢኖራቸውም የዛሬው መጣጥፌ ትኩረት ባለፉት አራት አመታት ስለተስተዋሉ ስሁት መታጠፊያዎች መሆኑን እገልጻለሁ።

ሕወሓት ለ27 አመታት በበላይነት ይዞት ከነበረው ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ከውስጡ በወጡ የለውጥ ኃይሎችና ለተከታታይ ሶስትና አራት አመታት በተካሔዱ ሕዝባዊ አመጾች በልክህ ሁን ሲባል ኮሽታ ሳያሰማ ጅራቱን ቆልፎ ሾከክ ብሎ ወደ መማጸኛ ከተማው መቀሌ ሲመሽግ ለጤና እንዳልሆነ መጠርጠር ይገባ ነበር። ብዙም ሳይቆይ ልዩ ኃይሉን በስፋት ሲያሰለጥን፤ ሚሊሻውን እስከ አፍንጫው ሲያስታጥቅ፤ የጦርነት ድቤውን ሲደልቅ፤ ምድርን አርባ እየገረፈ ጦር አውርድ ሲል፤ በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ የሰሜን ዕዝን ሲተናኮል ምን ሊመጣና ሊከተል እንደሚችል ገምቶና ተንትኖ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ይገባ ነበር። የሕወሓትን ማንነትና ባህሪ አውቆ ቅድመ ጥንቃቄና ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ባለመቻሉ በምንም የማይተመን ዋጋ አስከፍሎናል።

ይሄን ስል የደህንነትና የመከላከያ መዋቅሩ በሕወሓት እጅ ከወርች መቀየዱን አጥቼው አይደለም። ወይም አበው ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው የሚሉትን ወርቅ ይትበህልም ዘንግቸው አይደለም። ሆኖም ውስን በሆነው የወታደራዊና የሲቪል ደህንነቱ አቅምም ቢሆንም ለሰሜን ዕዝ የተደገሰለትን ታሪክም ትውልድም ይቅር የማይለውን ክህደትና ጭፍጨፋ ቀድሞ አውቆ የማንቂያ ደወሉን መንካት ቢቻል ኖሮ ጉዳቶን ሙሉ በሙሉ ማስቀረት እንኳ ባይቻል መቀነስ ይቻል ነበር የሚል ቁጭት ይሰማኛል።

በሰሜን ዕዝ በተፈጸመው ጭፍጨፋና ክህደት የተነሳ መንግስት ተገዶ የገባበትን ጦርነት እጅን በአፍ ባስጫነ ድል ሶስት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ መቀሌ በመግባት የሕወሓትን ከፍተኛ ፖለቲካዊና ወታደራዊ አመራር መደምሰስና መማረክ ቢቻልም፤ ድሉን ማስጠበቅ፣ ማጽናትና ማዝለቅ አልተቻለም። ችግሩ በጥናትና በግምገማ ተለይቶና ተረጋግጦ ይፋ ባይሆንም በውስንነትና በስሁት መታጠፊያነት ወይም በተሳሳተ ውሳኔነት የተረዳኋቸውን አንድ አንድ ነጥቦች ላንሳ። ከፍ ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርሁት የመንግስት አብዛኛዎቹ ውሳኔዎች በመርህ ደረጃ ትክክል ቢሆኑም የሕወሓትን ማንነትና ባህሪ ግን ከግምት ያስገቡ አልነበሩም። ክልሉ ነጻ ከወጣ በኋላ ለተወሰነ ጊዜ በኮማንድ ፖስት መተዳደር ሲገባው እንደ ንግድ ኩባንያ በዋና ስራ አስፈጻሚ እንዲመራ መደረጉ ጊዜያዊ አስተዳደሩ በቀላሉ በሕወሓት ደባ እንዲጠለፍ አስችሏል። በዚህ ላይ ሕግን ከማስከበር ዘመቻው ጎን ለጎን የትግራዋይን ልብ ለመማረክና የመረጃ ጦርነቱን ለማሸነፍ የተቀናጀ ርብርብ ባለመደረጉ ድክመቱን አባብሶታል። በአለማቀፍ ሚዲያውና ዲፕሎማሲው ሕወሓት ብልጫ ማግኘቱ በስንት መስዋዕትነት የተገኘውን ወታደራዊ ድል ለመጣል ተገደናል። የሚያሳዝነው ዛሬም ሕወሓትንና ጭፍሮቹን በልካቸው ትኩረት አለመስጠታችን ነው።

መንግስት ለሰብዓዊነትና ገበሬው እንዲያርስ፤ የትግራይ ሕዝብም የጥሞና ጊዜ እንዲኖረው ከትግራይ ክልል ለቆ ሲወጣ ተገቢውን ጥንቃቄና ዝግጅት ባለማድረጉና እንደ ኤርትራ ካሉ የክፉ ቀን አጋሮቹ ጋር መምከርና የመውጫ ስትራቴጂ መተለም ሲገባው ለምዕራባውያን ከክልሉ ለቆ እንደሚወጣ ከወር በፊት ማሳወቁ፤ ሕወሓት መረጃ ስለደረሰው ህቡዕ የገባውንና የተበተነውን ኃይሉን አሰባስቦ፤ ጥርሱን የነቀለበትን ደባ አክሎ ከክልሉ በመውጣት ላይ የነበረውን ሰራዊት ከማጥቃት ባሻገር የተወሰኑትን በመቁረጥና በሰላማዊ ሰዎች መንገድ በማዘጋት ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ተጠቅሞበታል።

በዚህ የልብ ልብ የተሰማው ሕወሓት በምዕራባውያን በሚደረግለት የሳተላይት፣ የሚዲያና የዲፕሎማሲ ድጋፍ በመታገዝ በሕዝባዊ ማዕበል አጎራባች የአማራና የአፋር ክልሎች የፈጸመው ሰቆቃ፣ ዘረፋና ውድመት መቼም ቢሆን ታሪክና ትውልድ አይረሳውም። ከሁሉም የአገራችንን የግዛት አንድነትና ህልውና ክፉኛ ፈትኗል። ሕወሓት የአዲስ አበባን አየር ጣርማ በር ላይ ሆኖ መማግ ቢችልም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር በሁሉም ግንባሮች በመገኘት ከወታደራዊ አመራሮች ጋር በሰጡት በሳል አመራር በሶስት ሳምንት ውስጥ ከፍተኛ ወታደራዊና ሞራላዊ ኪሳራ ተከናንቦ ትርፍራፊ ኃይሉን እያንጠባጠበ ሽምጥ ጋልቦ መማጸኛ ከተማው መቀሌ መሽጓል።

ሆኖም ሰራዊቱ አሁንም እስከ መጨረሻው ከመደምሰስ ይልቅ በትግራይ አጎራባች አካባቢዎች ግስጋሴው እንዲገታ መደረጉ ሕወሓትን ለ3ኛ ዙር ጦርነት ድቤውን እንዲደልቅ የልብ ልብ ሰጥቶታል። ሌላው ስሁት መታጠፊያ እነ ስብሀት ክሳቸው ተቋርጦ ከእስር የተለቀቁበት በትክክለኛው ሰዓት አለመሆኑ በአገራዊ አንድነቱ ላይ ከፍተኛ ዋጋ አስከፍሎናል። በዲያስፖራውም ሆነ በአገር ቤት ተፈጥሮ የነበረውን አንድነትም ክፉኛ ጎድቶታል። እንግዲህ አሁንም ተገደን ወደ ጦርነት የምንገባ ከሆነ ከአንድም ሁለት ጊዜ ከፈጸምናቸው ስህተቶች በደንብ መማርና ለ3ኛ ጊዜ ላለመድገም አበክረን መዘጋጀት አለብን። ሌላው ለውጡንም ሆነ ብልጽግናን አመድ አፋሽና እጀ ሰባራ ያደረገው የኦነግ/ሸኔ ነገር ነው።

በለውጡ ማግስት ከተወሰዱ ደፋር እርምጃዎች ወይም ውሳኔዎች አንዱ በአሸባሪነት ተፈርጀው በጎረቤት አገራት ነፍጥ አንስተው በትጥቅ ላይ የነበሩ ተቃዋሚዎች በለውጥ ኃይሉ ከቅንነት በመነጨ ችኮላ ባልሰከነ ድርድርና ቅድመ ሁኔታ ወደ አገር ገብተው ሰላማዊ ትግል እንዲያደርጉ መፈቀዱ ሌላው ስሁት መታጠፊያ ነው። ይህን ውሳኔ እንደ መልካም አጋጣሚ በመውሰድ በተለይ ኦነግ/ሸኔ በአውሮፕላንና በአውቶብስ ወደ መሐል አገር ገብቶ ትጥቅ አልፈታም እስከ ማለት በመድረስ ገና በሁለት እግሩ ያልቆመን መንግስት መገዳደር ጀመረ። በተለይ በኦሮሚያ ክልል ከሚቀሰቀሱ ሁከቶችና ግጭቶች ጀርባ እጁ እንዳለበት ተደጋግሞ ይነሳ ጀመር። በምዕራብ ወለጋ፣ በጉጂና በቦረና ዞኖች የንጹሐን ግድያ፣ ጠለፋና ዘረፋ ተባብሶ ቀጠለ። አባ ቶርቤ በመባል የሚታወቀው ገዳይ ክንፉም የኦሮሚያ አመራሮችን መግደል ጀመረ። የሞት ማስፈራሪያና ዛቻ በመላክ ታዋቂ ግለሰቦችንና አመራሮችን ማሸማቀቅን አጠናክሮ ቀጠለ።

ከጊዜ ወደ ጊዜ በለውጥ ኃይሉና በኦነግ መካከል የተፈጠረው ልዩነት እየተባባሰና እየተካረረ መጣ። ሆኖም የለውጥ ኃይሉ በልበ ሰፊነት እየተካረረ የመጣው ልዩነት በውይይት በሰላም ለመፍታት ጥረት አድርጓል። ይሄ ትዕግስቱም ፍሬ ያፈራ መስሎ ነበር። በአባ ገዳዎችና በታዋቂ ሰዎች አሸማጋይነት አምቦ ላይ እርቅ ወረደ። ሆኖም ይሄ እርቅ በሕግ የታገዘና አስገዳጅ ስላልነበር ብዙም ሳይቆይ ፈረሰና መካሰስ ተጀመረ። የለውጥ ኃይሉ ከኦነግ ጋር ያለውን ልዩነት በሰላም ለመፍታት የሄደበት እርቀት ለሴራ ትንተናና ለጥርጣሬ እየዳረገው መጣ። ቁጥሩ ቀላል ያልሆነ የለውጡ ደጋፊም በመንግስት የአባባይነትና የልምምጥ አቋም ላይ ጥያቄ ማንሳት ጀመረ። የኦነግ/ሸኔ ታጣቂዎች ማንነትን እየለዩ ንጹሐን መጨፍጨፍ፣ ማፈናቀልና መዝረፍን አባብሰው ሲቀጥሉ በለውጥ ኃይሉ ላይ እምነት የማጣት ነገር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጣ።

አዲስ አበባ የተቀመጠው ኦነግም በስሙ እየተፈጸመ ያለው ጭፍጨፋ እሱን እንደማይወክልና ከደሙ ንጹሕ መሆኑን ቢለፍፍም በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም ነበር። ራሱን ሸኔ ብሎ የሚጠራው ወታደራዊ ክንፍም ጥቃቱን በማስፋት በኦሮሞ ሕዝብ ላይም ሕልቆ መሳፍርት የሌለው ግፍ መፈጸሙን አባብሶ በመቀጠል የሚቃወሙትን አባ ገዳዎች፣ የአገር ሽማግሌዎችና ታዋቂ ሰዎች ማሳደድና መግደል ጀመረ። በርካታ የኦሮሚያ ብልጽግና አመራሮችን ገደለ። በኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎችም ተጠናክሮ ነጻ መሬት እስከመቆጣጠርና መዋቅርን እስከመያዝ በመድረስ ዕንቅስቃሴን እስከመግታት ደረሰ።

ሕወሓት በሰሜን ዕዝ ላይ ክህደትና ጭፍጨፋ በመፈጸሙ መንግስት ተገዶ ወደ ጦርነት ሲገባ ሸኔ አጋጣሚውን በመጠቀም እየተጠናከረ በመምጣት በስፋት መንቀሳቀስ ጀመረ። እንደሱ በአሸባሪነት ከተፈረጀው ሕወሓት ጋርና ከሌሎች ታጣቂዎች ጋር በመቀናጀት እዚህም እዚያም በንጹሐን ላይ የሚፈጽመውን ጭፍጨፋ አጠናክሮ ቀጠለ። ከመንግስት የጸጥታ ኃይሎች ጋር ፊት ለፊት መግጠም ጀመረ። በኋላ ደግሞ ከአሸባሪው ሕወሓት ጋር ግንባር በመፍጠር መንግስትን በኃይል ለመለወጥ ተንቀሳቀሰ። ዛሬም በተበታተነ ሁኔታ ቢሆንም የደህንነትና የጸጥታ ስጋት መሆኑ እንደቀጠለ ነው።

የትጥቅ ትግል ላይ በቆየባቸው በርካታ አስር አመታት አንዲት ጎጥ ተቆጣጥሮ የማያውቀው ይህ ቡድን እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰው የለውጥ ኃይሉ ያለ አስገዳጅ ድርድርና ስምምነት ወደ አገር እንዲገባ ስላደረገ ነው። የለውጥ ኃይሉ ልዩነቶችና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች በሰለጠነ ሰላማዊ ትግል ሊፈቱና ሊመለሱ ይችላሉ በሚል ቅንነት በአሸባሪነት ተፈርጀው የነበሩ ድርጅቶች ወደ አገር እንዲገቡ ያሳለፈው ውሳኔ በመርህ ደረጃ ትክክል ቢሆንም በስርዓትና በድርድር የተቋጨ ስላልነበር ውድ ዋጋ አስከፍሎናል። እያስከፈለንም ይገኛል። ስሁት መታጠፊያዎች ወይም ውሳኔዎች ከአሰብነው መዳረሻ ወይም ግብ እንዳንደርስ አርጎናል የምለው ለዚህ ነው።

ስህተት እንደ ቡና አቦል፣ 2ኛና በረካ የለውምና ብንችል ከታሪክና ከሌሎች ስህተት እንማር፤ ካልቻልን ደግሞ ከስህተታችን በጊዜ እንማር። እርግጠኛ ነኝ መንግስት ሕወሓት ለ3ኛ ጊዜ ጦርነት ቢከፍት በሚል ከቀደሙ ስህተቶቹና ስሁት መታጠፊያዎቹ ተምሮ፤ ከሕወሓትም ሆነ ከቡችላዎቹ ቀድሞ ለማሰብና ለመንቀሳቀስ ዝግጁ ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !

አሜን።

# ወቅታዊ

## ‹‹የዚህ አገር ችግር መሠረታዊ ምንጩ፤ የፖለቲካ ሊሂቃን ናቸው››

**አቶ ትዕዛዙ አያሌው**
**በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር**

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

ፖለቲካ ማለት በቡድን ያሉ ግለሰቦች የጋራ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚያስችላቸው ሂደት ነው። በዚህ ምክንያት ምንም እንኳ ፖለቲካ የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ከአገርና ከመንግሥት ጋር የተገናኘ ቢሆንም በሌላ አንጻር የሰው ልጆች በቡድን ሆነው በሚገኙበት ማናቸውም ስብስብ ይገኛል፣ ለምሳሌ በኩባንያዎች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በሃይማኖት መዋቅሮች፣ በቤተሰቦች ውስጥ ሳይቀር ፖለቲካ አለ። የኃይል አመዳደብ፣ የቁጥጥር፣ የውሳኔ ላይ መድረስ፣ የምጣኔ ሃብት ክፍፍል ጥያቄዎች በሁለትና ከዚያ በላይ ባሉ ሰዎች መካከል ሲነሱ ያንን ጥያቄ ለመፍታት በሚደረግ ሂደት፣ በዚያ ፖለቲካ አለ። ከዚህ አንጻር በአንዳንዶች አስተሳሰብ አብዮት፣ ጦርነት፣ ማህበረሰባዊ ግጭት ፖለቲካ ሳይሆኑ የፖለቲካ ሂደቱ ክሽፈት ናቸው። በሌሎች አስተያየት እኒህም የአጠቃላይ ሂደቱ አካል ስለሆኑ እንደ ፖለቲካ ይወሰዳሉ ሲል ዊኪፒዲያ ስለ ፖለቲካ ምንነት ይተነትናል፡።

ፖለቲካ ይህ ከሆነ ዘንዳ አንዳንድ ምሁራን ደግሞ ስለ ኢትዮጵያ ፖለቲካ እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል። ፖለቲካችን ከሽኩቻ፣ ከጥሎ ማለፍ እና ሴራ አልተላቀቀም። ቅንነት የሌለበት የሕይወት እንቅስቃሴ ሁሉ ጨው የሌለው ወጥ እንደማለት ነው። ነገራችንን ሁሉ አያጣፍጠውም።

ኢትዮጵያውያን በባህሪያችን በሌሎች ላይ መፍረድ ልማዳችን ነው። አትፍረድ ይፈረድብሃል፤ ባልንጀራህን ከራስህ አስበልጠህ ውደድ፤ ሁለት ካለህ አንዱን አካፍል ወዘተ.... የሚሉት የአምላክ መመሪያዎች ብዙም ትኩረት የሰጠናቸው አይደሉም፤ እናም ሁልጊዜ ነገሮችን የምንረዳበት መነጽር ሁሉ ከነባራዊ ሁኔታዎች (ለምሳሌ ከጊዜ፣ ከቦታ፣ ከሁኔታ) አንጻር ሳይሆን ከራሳችን ፍላጎት አንጻር ነው።

ነገራችንን ስንመዝን ከራሳችን ድክመት ወይም ጥንካሬ አንጻር ሳይሆን በቅርባችን ካለ፣ ከምናውቃቸው ሰዎች ነው። ኑሯችን ሁሉ ከራሳችን ጋር ሳይሆን በሌሎች ሕይወት ውስጥ ነው። በዚህም ነው በነገራችን ሁሉ መሻሻሉን ለማምጣት እንድንችል መሠረታዊ የሆነው የራስን ድክመትና ጥንካሬ ማወቅ ፍላጎቱንም አቅሙንም ያጣነነው። የዚህ ውጤት ወይም ነጸብራቅ ደግሞ ዘወትር በማያልቅና አላአስፈሊጊ ፉክክር ወይም ሽኩቻ ውስጥ መሆናችን ነው። እኔስ ከማን አንሼ የሕይወት መመሪያችን ነው። የአንዳችን ማሸነፍ የሌላችን መሸነፍ፤ የአንዱ መሻል የሌላው መቆርቆር፤ የአንዱ ማግኘት የሌላው ማጣት፤ የአንዳችን ማግኘት የሌላው ማጣት ይመስለኛል ሲሉ አሁናዊ ፖለቲካው ይተነትኑታል።

የዛሬ የአዲስ ዘመን እንግዳ በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር የሆኑት አቶ ትዕዛዙ ናቸው። እርሳቸው የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ዳራ፣ የፖለቲካ ምንነትና የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ ብሎም የዓለም የፖለቲካ ጉዞ እና ኢትዮጵያ አካሄድን አስመልክቶ ሙያዊ ሃሳቦችን ሰንዝረዋል። መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፡- ወቅታዊ የኢትዮጵያን እና ዓለም አቀፉ ፖለቲካ ግንኙነት እንዴት ይመለከቱታል?**

**አቶ ትዕዛዙ፡-** በብዙ መንገድ ማየት ይቻላል። እንደሚታወቀው የውጭው ፖለቲካ ውስጣዊ ፖለቲካ ላይ የራሱ አስተዋፅኦ አለው። ውስጣዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴው ከውጭው ዓለም ጋር ለሚደረገው ግንኙነት የራሱ የሆነ አዎንታዊና አሉታዊ ትርጉም አለው። በአሁኑ ወቅ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የሚታወቅ ነው። እስካሁን ድረስ ያልተቋጨና ከአሸባሪ ሕወሓት ጋር ያለው ጦርነት አልተቋጨም። ዓለም አቀፉ ማህበረሰብም ከራሳቸው ብሔራዊ ጥቅምጋር በተያያዘ አቋም ይዘዋል። ተደጋግሞ ሲነገር እንደነበረው በአሁኑ ወቅት የአሜሪካ እና የምዕራባውያን አቋም ከኢትዮጵያ ጋር በተቃርኖ የቆመ ነው። ይህ የሚያሳየን ውስጣዊ የፖለቲካ ትኩሳታችንና ያለን ወቅታዊ ሁኔታ ከውጭው ዓለም ፖለቲካ ጋር በቀጥታ እንደሚገናኝ እንደማሳያ የሚወሰድ ነው።



ብዙውን ጊዜ የውጭ ግንኙነት የሚመሠረተው በአገራት ብሔራዊ ጥቅም ላይ ነው። መንግሥታትም የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያቸውን ሲያረቁ ከብሔራዊ ጥቅማቸው ጋር በተሳሰሰረ መንገድ ነው። የሕወሓትን አካሄድ ብንመለከት ምዕራበውያን የወገኑለት ቡድን ነው። ይህ ማለት ከምዕራባውያን ስትራቴጂክ ጥቅምና ፖሊሲ አኳያ አሁን ስልጣን ላይ ያለው መንግሥት የእነርሱን ብሔራዊ ጥቅምና ስትራቴጂክ አጋርነት አያሳካም ብለው ስለሚያስቡ ይህን መሰል እና ድጋፍ ለሕወሓት እያደረጉ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። አሁን ያለንበት ሁኔታ የሚያሳየውና የሚያሳየው ፖለቲካዊ ምስልም ይህንኑ የሚያስረግጥ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ ሁኔታ ዓለም ለሁለት ጎራ የተከፈለ ነበር። በሌላ በኩል የዩክሬን ጉዳይ የዓለም ፖለቲካ ሽኩቻ ይታወቃል። የእነዚህ ድምር ውጤትስ?**

**አቶ ትዕዛዙ፡-** እንደአጠቃላይ ልዕለ ኃያላን የምንላቸው አገራትና መንግሥታት እርስ በእርስ የሚያደርጉት ሽኩቻ እኛ ዘንድ የሚያመጣው ጉዳትና ጥቅም አለ። የዩክሬን እና ራሺያ ጉዳይ ብንመለከት የልዕለ ኃያላን አገራት በጥቅም ላይ የሚያደርጉት ሽኩቻ ነው።

ይህ ለኢትዮጵያ ይዞ የመጣው ጥቅም ቢኖር ምዕራባውያን ለጊዜውም ቢሆን ዓይናቸውን ከኢትዮጵያ ላይ ነቅለው ወደ ዩክሬንና ራሺያ ትኩረት አድርገዋል። እኛ ግን ይህን ክፍተት መጠቀም አለብን። በርካታ የፖለቲካል ሳይንስ ምሁራንም የሚመክሩት ይህንኑ ነው። መንግሥትም

> **በአሁኑ ወቅት ቻይና ፣ሩሲያ፣ ቱርክ፣ ሕንድ እና ሌሎች ሀገራት በሁሉም ዘርፍ በመጉሳት ወደፊት እየመጡ ነው:: በዚህም የአሜሪካን የበላይነት ፈተና ውስጥ እያስገቡት ነው:: ይህ ኢትዮጵያን ጨምሮ ለበርካታ ሀገራት እንደ መልካም አጋጣሚ ወይንም ተጠቃሚነት ሊወሰድ ይችላል**

በፍጥነት መሥራት የሚገባውን ሥራ መሥራት አለበት የሚል አቋም አለ።

በንፅፅር ምዕራባውያንና አሜሪካ ከእኛ ጋር ስትራቴጂክ ጥቅም የላቸውም ማለት አይደለም። ነገር ግን የዩክሬን ጉዳይ ጊዜ የማይሰጣቸውና እጅግ እንቅልፍ የነሳቸው በመሆኑ ትኩረታቸውን በሙሉ ወደዚያ አድርገዋል። በዚህ አጋጣሚ አቅማቸውን ለማሳየትና ራሺያን ለማዳከም የሚጣጣሩበት ወቅት እንደሆነ በግልፅ እየታየ ነው። ምዕራባውያን በመተባበር እና አሜሪካ በበላይነት እየመሩት ባለው በዚህ ፖለቲካዊ ዘመቻ በዓለም ላይ የሚደረገውን እየተመለከትን ነው። በዚህ የጦርነት ወቅት ለዩክሬን ያልተደረገ ድጋፍ የለም። በገፍ የጦር መሳሪያ ወደ ዩክሬን እየጓጓዘ ነው። በቀጥታ በጦርነቱ ላይ እየተሳተፉ ነው ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር ቢከብድም ማዕቀብ በማዕቀብ ላይ እየጣሉ ራሺያን ለማዳከም እየሠሩ ነው። ይህ ሁሉ የሆነው ኃያላን በፈጠሩት ሽኩቻ ሲሆን በድሃ አገራት ላይ ደግሞ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ መሆኑ ግልጽ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን በሚስተዋለው የዓለም የፖለቲካ ሚዛን ውስጥ ኢትዮጵያ ተጠቃሚ ናት ወይስ ተጎጂ?**

**አቶ ትዕዛዙ፡-** አሁን የሚስተዋለው የዓለም የፖለቲካ ትግልና አካሄድ ዓለምን ያልተማከለ ወደ ሆነ ዓለም እየወሰዳት ስለመሆኑ በርካቶች እየተናገሩ ነው። ለበርካታ ዓመታት በዓለም የኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ እና የጦር ሚና ላይ አሜሪካ በብቸኝነት እየመራች ነበር። በዚህ ውስጥ ወዳጅ ናቸው፤ ለእኔ አካሄድም ይበጁኛል ያለቻቸው ምዕራባውያንን በማስከተል ብዙውን ነገር ስትቆጣጠር፤ በብቸኝነት ፈላጭ ቆራጭ ሆና ቆይታለች። በዚህ ዓለምን እንደአንድ አድርጎ የመቆጣጠርና የመግዛት አዝማሚያዎችና ፍላጎቶች በሰፊው ሲንፀባረቁ ኖረዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የአሜሪካን የኃይል ሚዛን የሚገዳደሩና የምዕራባውያንን አለንባይነት የሚፈታተኑ ፖለቲካ ኃይል ሚዛን በእጅጉ እየጎላ ነው። ይህ ደግሞ አሜሪካ ዓለምን በብቸኝነት ለመቆጣጠርና ለመምራት በምታደርገው ጥረት ላይ ትልቅ አደጋ የጣለ አድርጋ የምትወስድ መሆኑ ግልፅ ነው። በየአቅጣጫው በዓለም ላይ ተገዳዳሪ የሆኑ ኃይሎች እየተበራከቱና ለብሔራዊ ጥቅማቸው በሚበጃቸው መንገድ ጎራም እየፈጠሩ ነው። ታዲያ ይህ በዓለም የፖለቲካ አሰላለፍና አወቃቀር ላይም የራሱ የሆነ አሻራ ጥሎ የማለፍ ዕድል እንደሚኖረውም የዘርፉ ምሁራን በተደጋጋሚ እየተናገሩ ነው።

በአሁኑ ወቅት ቻይና ፣ሩሲያ፣ ቱርክ፣ ሕንድ እና ሌሎች አገራት በሁሉም ዘርፍ በመጉላት ወደፊት እየመጡ ነው። በዚህም የአሜሪካን የበላይነት ፈተና ውስጥ እያስገቡት ነው። ይህ ኢትዮጵያን ጨምሮ ለበርካታ አገራት እንደ መልካም አጋጣሚ ወይንም ተጠቃሚነት ሊወሰድ ይችላል። ቀደም ሲል አሜሪካ በነበራት የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነት ዓለምን እንደፈለገችው ትጠመዝዝ ከነበረበት አካሄድ በተወሰነ መንገድ ለመራመድ ዕድል ይሰጣል የሚል እሳቤ አለ። አሁን አጋር ኃይሎችን ለመጠቀም ዕድል ይሰጣል። ለአብነት በትግራይ ክልል በነበረው የሕግ ማስከበር ዘመቻ አሜሪካ ፈቃደኛ ባትሆንም የጦር መሳሪያ ከአሜሪካ ውጭ ከሆኑ እንደ ቱርክና የአረብ አገራት ስናገኝ ነበር። ይህ ከጥቅሞቹ እንደ አንዱ መወሰድ ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ ዓለም አቀፍ ፖለቲካ ግንኙነትና አካሄድ ጉዳት አያመጣም?**

**አቶ ትዕዛዙ፡-** የለውም ብሎ መደምደም አይቻልም። ዓለም ሲከፋፈል አለመረጋጋት ይዞ ይመጣል። የተከፋፈለ ዓለም ነው ያለው። ስለዚህ ግንኙነቶች በጣም የመስፋፋት እና የግጭት መስፋፋትም በዚያው ልክ ሊኖር ይችላል። ይህም የኢኮኖሚና ሰላም መናጋት ያመጣል። አንዱ የዓለም ክፍል ሲቃወስ ሌላውም በዚያው ልክ ይቃወሳል። ለአብነት በአሁኑ ወቅት በዩክሬን እና ራሺያ መካከል ያለውን ቀውስ ብንመለከት ዓለምን እያናጋው ይገኛል። በዚህ ዘንዳ ካየነው ጉዳቱ የከፋ የመሆን ዕድልም ይኖረዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ከዓለም አቀፉ ፖለቲካ ግንኙነትና አካሄድ በመረዳት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ**

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ



> **ፖለቲከኞቻችን የችግሩ መንስኤ ከሆኑ ዋንኛው ነገር የዓለምን እና አገራዊ ሁኔታ ተረድተውት የፖለቲካ ፕሮግራም ቀርፀው እየተንቀሳቀሱ አይደለም ማለት ነው:: ዘመናዊ ፖለቲካ ተጀመረበት ብለን የምናስበው 1960ዎቹ እንኳን ብናይ ከጅምሩ የፖለቲካ አካሄዳቸውን ብናይ የፖለቲካ ዕይታቸው፣ ፍልስፍናቸው የተወሰደው ከውጭ ነው:: በወቅቱ ከዓለም ፖለቲካ ላይ ነግሶ የነበረውን ሌኒንዝም፣ ሶሻሊዝም በቀጥታ በመውሰድ ለመተግበር የሚደረግ ሙከራ ነበር**

**የፖለቲካ ፓርቲዎች በኃላፊነት እየተንቀሳቀሱ ነው ማለት ይቻላል?**

**አቶ ትዕዛዙ፡-** በዓለም ላይ ያለውን የፖለቲካ ጎራ፣ አካሄድ እና ጫና በሚገባ መረዳት፣ መተንተንና መተንበይ ያስፈልጋል። በአጠቃላይ ታሪካዊ ዳራዎችን፣ አሁናዊ ሁኔታዎችንና የነገ ቢሆኖችን መገምገምና መረዳት ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የፖለቲከኞች፣ የመንግሥትና የዘርፉ ባለሙያዎች ኃላፊነት ነው። ነገሮችን በሚገባ መረዳትና ቁርጥ ያለ የፖለቲካ ማዕቀፍ ይዞ መንቀሳቀስ ይገባል። የፖለቲካ ሜዳውን ማወቅና መሠረታዊ ሥራቸውም መሆን አለበት፡ አንድ ፖለቲካ ውስጥ የሚሳተፍ ሰው በተደራጀ መንገድ ፖለቲካን መሥራት የለበትም። ይህን ካለመረዳት የተነሳ በአገራችን ችግሮች ይስተዋላሉ።

በፖለቲካው ዓለም ከእኛ ጋር ስትራቴጂክ አጋር የምንላቸው እነማን ናቸው የሚለውን ማወቅ ይገባል። በዓለም ፖለቲካ ተጠቃሚ የሚያደርገን አካሄድ የቱ ነው የሚለውን ማወቅ ብሎም ሕዝብን በዚያው ልክ ማንቀሳቀስ ተገቢ ነው። ይህን እያደረጉ ነው ወይ የሚለውን ካነሳን በአንድም ይሁን በሌላው መልኩ እዚህ አገር በተለይም ስለ ፓርቲ ፖለቲካ ማውራት ከጀመርን ወዲህ በተለይም ከ1960ዎቹ የጀመረ ነው።

አብዛኞቹ ችግሮቻችን የሚመነጩት ከፖለቲከኞቻችን ነው ብንል ማጋነን አይመስለኝም። ፖለቲከኞቻችን የችግሩ መንስኤ ከሆኑ ዋንኛው ነገር የዓለምን እና አገራዊ ሁኔታ ተረድተውት የፖለቲካ ፕሮግራም ቀርፀው እየተንቀሳቀሱ አይደለም ማለት ነው። ዘመናዊ ፖለቲካ ተጀመረበት ብለን የምናስበው 1960ዎቹ እንኳን ብናይ ከጅምሩ የፖለቲካ አካሄዳቸውን ብናይ የፖለቲካ ዕይታቸው፣ ፍልስፍናቸው የተወሰደው ከውጭ ነው። በወቅቱ ከዓለም ፖለቲካ ላይ ነግሶ የነበረውን ሌኒንዝም፣ ሶሻሊዝም በቀጥታ በመውሰድ ለመተግበር የሚደረግ ሙከራ ነበር።

ስለዚህ የዓለምና አገር ውስጥ ፖለቲካን በደንብ ባጣጣመ መንገድ መረዳትና ያንን ማስኬድ ላይ ችግር ነበር ማለት ነው። ያኔ አብዛኛው የሚስተዋለው መፍትሄ ከማምጣት ይልቅ ችግር ፈጣሪ ነበር። አይደለም ለአገሪቱ መጥቀም ቀርቶ እርስ በእርስ የሚጠፋፉ ሆነው ነው የተገኙት። ህልውናቸው እንዳይኖርም ያደረገ ነው። በመሆኑም የሕዝብና አገርን አጠቃላይ ሁኔታ ልትረዳ ከሆነ መሰል አዙሪት ውስጥ መልሶ የሚጥለን ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡-በኢትዮጵያ ውስጥ ግጭቶች አሉ። ይሄን አስመልክቶ በየክልሉና በየከተማው የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች መግለጫዎችን ያወጣሉ። ሕዝባዊና አገራዊ አንድነት የሚያስጠብቁና ችግሮችን የሚቃልሉ ናቸው ብለው ያስባሉ?**

**አቶ ትዕዛዙ፡-** የዚህ አገር ችግር መሠረታዊ ምንጩ የፖለቲካ ልሂቃን ናቸው። የችግሩ ፈጣሪ ፖለቲከኞች ናቸው። ይህ ደግሞ የሚመነጨው ከሚከተሉት ፖለቲካ ፕሮግራም ነው። እዚህ አገር ዋነኛ የፖለቲካ መሰባሰቢያ መድረክ ዘውግ ወይንም ብሔርተኝነት ነው። ይህ ደግሞ የተመሠረተው ደግሞ የብሔርን ፖለቲካ ገዢ ሃሳብ አድርጎ ያስቀመጠው ሕገመንግሥቱ ነው። አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስልጣን ላይ ያለው ጭምር የብሔር ፖለቲካ ላይ ያተኮረ ነው። አንዱ ፓርቲ ለሆነ ብሔር ብቻ የቆመ ነው። አንዱ ከሌላው በተቃርኖ የቆመበት ፖለቲካና ሃሳብ ነው። ሁላቸውንም ብናይ ታሪክ የሚረዱበት፤ አንዱ አንዱ ፓርቲ ከሌላው ጋር ሲታይ ያላቸው የፓርቲ ራዕይ ሙሉ ለሙሉ የሚጋጭ፤ አንዱ ከሌላቸው በሐሳብም የማይስማማ ነው። አይደለም አብሮ ለመስራት ቀርቶ ሌላው አንደኛው አድራጊ ፈጣሪ ሆኖ ሌላውን ለማጥፋት የሚሠራ ነው የሚመስለው። በመሆኑም የፖለቲካው ችግር ምንጭ የፖለቲካው ልሂቃን ናቸው። ስለዚህ ይህ መቅረት አለበት። ሕገመንግሥቱን ጨምሮ በዚህ መንገድ በፖለቲካ መደራጀትን በሕግ ማዕቀፍ መልክ ማስያዝ ይገባል። የአገሪቱን የረጅም ጉዞ የሚያመላክትና በጋራ ለመኖር የሚያስችል እንጂ እርስ በእርስ የሚጠፋፋ መልክ ይዞ መኬድ የለበትም። ይህ በጊዜ ካልተስተካከለ ለአገሪቱም አይጠቀምም። አገሪቱ ውስጥ የሚገኘውን የፖለቲካ አደጃጀትና ቀጣይ ዘመናትን ዕጣ ፈንታ ከግምት ውስጥ ያስገባ ሥርዓትና የፖለቲካ ስሪት መፍጠር ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ መሠረታዊ ችግር በሰነድ የተደገፈ ፖለቲካዊ ሥርዓትን የመተግበር ችግር ወይስ ያልተከሰተን የፖለቲካ ሰነድ መፍጠር?**

**አቶ ትዕዛዙ፡-** ሁለቱም ናቸው ብዬ አስባለሁ። በአንድ መልኩ ተግባር ዝም ብሎ አይመጣም። መነሻው ሃሳብ ነው። ሃሳብ የፖለቲካ ፓርቲ መነሻ ይሆንና ወደ ተግባር ይገባል። የእኛ አገር የብሔር ጽንፈኝነት መሠረታዊ ችግሩ ነው። ከዚህ በፊት የነበረው ሕወሓትና መሰሎቹ ይዘውት የመጡት ትርክት ነው። በሌላ በኩል የትግበራ ችግር ነው። ሌላው ቀርቶ ራሳቸው አልተገዙበትም። ሕጉ በራሱ ችግር የለበትም የአፈፃፀም እንጂ ይባላል።

መጀመሪያ መቅደም ያለበት ብሔራዊ ጥቅም ነው። እያንዳንዱ ጥያቄዎች የሚስተናገዱበትን ማበጀት የሚቻለው በዚህ ነው። ነገር ግን እዚህ አገር የሚደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች መጀመሪያ የሚያተኩሩት የወጡበት ብሔር እና ቋንቋ እንጂ አገር ላይ አይደለም።

ኢትዮጵያ የሚለውን በሁለተኛ ደረጃ የሚይዙ ናቸው። ሕወሓትና መሰሎቹ በዚህ ደረጃ አውርደውታል። ከኢትዮጵያ ህልውና በተቃራኒና በግብታዊነት የቆሙ ናቸው። አገራዊ የፖለቲካ ስትራቴጂ የላቸውም። ኢትዮጵያ እኛን ካልጠቀመች እንደፈለገች ትሁን የሚል ነው። ይህ ደግሞ በግልጽ ሕገመንግሥታዊ ድጋፍ ስላላቸው አይፈረድባቸውም። በመሆኑም ይህን ማስተካከል ያስፈልጋል። በመሆኑም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ችግር የትግበራ ብቻ ሳይሆን የሕግ አለመሻሻል እና ጥሩ አለመሆን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ፖለቲከኞችንና ፓርቲያቸውን ስብስብ እንዴት ይመለከቱታል?**

**አቶ ትዕዛዙ፡-** መሠረታዊ ነገሩ ይህ ነው። የዘመናዊ ፖለቲካ፤ ዴሞክራሲና መሰል ነገሮች የቅርብ ጊዜ ናቸው። ለዚህ ልምድና ባህሉ የለንም። በአፍሪካ አገራት አኳያም ገና ብዙ ይቀረናል። ገና የ50 ዓመት ልምድ ነው። ፖለቲከኞች ወደ ፖለቲካ እና ፓርቲ የሚገቡት መጀመሪያ ዓላማው ሕዝብን ማገልገል ነው፤ ምንም እንኳን ፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ መታገያ ስልት ቢሆንም። አስቀድሞ የሚታሰበው ግን አገርን መጥቀምና ሕዝብ ማገልገል ነው። ነገር ግን እዚህ አገር በተጨባጭ የሚታየው ብዙዎች ፓርቲዎች ሆኑ በግለሰብ የሚሳተፉት የግልና የተወሰነ ቡድን ብቻ ለመጠቅም ሲሠሩ፤ ሲያሴሩ፤ እርስ በእርስም ሲጠፋፉ እናያለን።

ተመሳሳይ ፖለቲካ አይዶሎጂ ኖሯቸው እንኳን አንዱ ሌላውን ያጠፋል። መኤሶን እና ኢህአፓን ብንመለከት በብዙ ነገር ተመሳሳይ ነበሩ። ፖለቲካችን ከሽኩቻ፣ ከጥሎ ማለፍ እና ሴራ ያልተላቀቀው በምንም ሳይሆን በልሂቃኖቻችን ባህሪያዊ ምክንያቶች ነው። የዚህ ሁሉ መሠረቱ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው አጥፊ የፖለቲካ ባህላችን የራሱ አስተዋጽኦ አለው። ይህም ልዩነቶችን በንግግር ሳይሆን ከሆነ በጠብ፣ በሴራ፣ ካልሆነ በኩርፊያ መፍታት ባህላችን መሆኑ ነው።

ነገር ግን በተወሰነ የግል ጥቅም እና የተሻልኩ ነኝ በሚል እርስ በእርስ በመጠፋፋትና ለአሁኑ ፖለቲካ መጥፎ ጠባሳ ጥለው አልፈዋል። በሕግ አለመመራት፤ አገር አለማስቀደም፤ ቁርጠኛ አለመሆን ችግሮች አሉ። እነዚህ ከተስተካከሉ ወደፊት የተሻለ ነገሮችን ማየት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ሸኔ እና መሰሎቹ የወጡበትን ብሔር ጭምር እየጎዱት ነው። ከዚህ አኳያስ የዘውጌ ፖለቲካ የራሱን ወገን በትክክል ይጠቅማል ማለት እንችላለን?**

**አቶ ትዕዛዙ፡-** እውነታውን ያለመረዳት ችግር ነው። እነርሱ እንደሚያስቡት አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ አመጣጥና አኗኗር ይታወቃል። የሕዝቡን ትስስር የተረዱ አይመስልም። አሁንም ከዱሮ እሳቤ አልወጡም። ሕወሓትን ማየት በቂ ነው። የትግራይ ሕዝብ ያለበትን የተመለከተ ሌላ ምሳሌ አይፈልግም። ሸኔም ከዚህ የተለየ ዕድል የለውም። አሁን የሚስተዋለውን አለመረጋጋት ከመፍጠር የዘለለ ምንም ለውጥ አያመጡም። የተወሰነ ቡድን ችግር ነው ብለው የወሰዱትን የኢትዮጵያ ችግር ነው ብለው ወስደዋል። ግን እነርሱ እንደ ትልቅ አጀንዳ ያነሱት ትንሽ ችግር ነው።

እዚህ አገር የበርካቶች ፍላጎት ተመሳሳይ ነው። በሁሉም ሕዝብ ዘንድ ልማት፤ ፍትህ እና ዴሞክራሲ ይፈልጋል። ነገር ግን እነዚህ ዘውጌ ፖለቲከኞች ብሔርን ወሰዱት እንደ ትልቁ የማታገያ ስልት አድርገው ነው። ይህ ማለት ደግሞ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ችግሮችን የመተንተን የማወቅና ማስተካከል አቅማቸው አነስተኛ መሆኑን ያሳያል።

**አዲስ ዘመን፡- ሸኔን የመሳሰሉ አካላት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እርስ በእርስ መከፋፈል መጀመራቸውም በሚዲያ ሰምተናል። ይህ ለምን የሆነ ይመስሉታል?**

**አቶ ትዕዛዙ፡-**በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ የሆነ የሕዝብ መሰላቸት አለ። በሕዝቡ ላይ የሚያደርሱት እንግልትና በደል በጣም ጫፍ እየነካ ነው። የሚያመጡት ለውጥም እንደሌለ የተረዱ ይመስለኛል። ከአገር ውስጥና ከውጭ ሆነው አገር ለማፍረስ ከሚሠሩት ጋር ተናበው ቢሠሩም ምንም ሊያመጡ አልቻሉም። በመሆኑም በራሳቸው ሥራ የተሰላቹና ተስፋ የቆረጡ ይመስለኛል። ከዚህ በኋላ ያለውን ሕዝባዊ ጫና መቋቋም የሚቻላቸው አለመሆኑንም ይገነዘቡታል።

በዚህ ወቅት ግን በርካታ ሥራዎች መሠራት አለባቸው። በእነዚህ ቡድኖች መካከል የተፈጠረውን ሁኔታ ማጤን ያስፈልጋል። መንግሥት ክፍተቶችን በመጠቀም የተጠናከረ ሥራ መሥራት አለበት። በአሁኑ ወቅት እንደ አገር ሰፊ ችግር ውስጥ በመሆናችን ለመፍትሄ መሥራት አለብን። የሚወሰደው እርምጃም አስተማሪ እንዲሆን በተደጋጋሚ ሊታሰብበት ግድ ይላል። ሕዝብና መንግሥት የሚገኙትን ዕድል መጠቀም አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡-የዝግጅት ክፍላችን እንግዳ ሆነው ሙያዊ ሐሳብዎትን ስላካፈሉን እናመሰግናለን።**

**አቶ ትዕዛዙ፡-** እኔም ሐሳቤን እንዳካፍል ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ!

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ለአገር ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ እያደረገ ያለ ጋርመንት

**አሥመረት ብሥራት**

"ኢትዮጵያ ታምርት" በሚል መሪ ቃል የአዲስ አበባ የስራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት አምራቾችን አቅም የማሳደገያ የምክክርና ንቅናቄ መድረክ በቅርቡ በአዲስ አበባ ተካሂዷል። መድረኩ የከተማዋን አምራች ኢንዱስትሪዎች አቅም ለማጎልበት ያቀደ እንዲሁም ችግሮቻቸውን አዳምጦ መፍታትን ያለመ ነው።

መድረኩ በተካሄደበት እለት ማልዶ በቦታው የተገኘው የመድረኩ ታዳሚ ውጤታማ የተባሉትን መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን እንዲጎበኝ ተደርጓል። በአዲስ አበባ አራዳ ክፍለ ከተማ ሳንፎርድ ትምህርት ቤት አካባቢ የሚገኝ ደረጃውን የጠበቀ፤ ከውጭ የሚገባውን ሶፋ መተካት በሚችል ደረጃ ሶፋ የሚያመረት ኢንዱስትሪን፣ በመቀጠልም በርካታ የሰው ሀይል በውስጡ ይዞ የሚያሰራ አንድ ጋርመንት ተጎብኝተዋል።

ከጉብኝቱ በኋላም ከታዳሚው ጋር ለመወያየት በተዘጋጀው መድረክ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባና የስራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ሀላፊ አቶ ዣንጥራር አባይ ባስተላለፉት የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክት በከተማዋ ከተያዘው እቅድ አንዱ «ኢትዮጵያ ታምርት» የሚለው ንቅናቄ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም ከፍ ለማድረግ እንደሚረዳ ተናግረዋል።

በተጨማሪም ንቅናቄው አሁን ላይ በከተማዋ ያሉትን 10 ሺህ 504 አምራች ኢንዱስትሪዎች በጥራትና ቁጥር ወደ 26 ሺህ 260 ለማሳደግ እንደሚረዳ አስገንዝበው፣ እነዚህ ኢንዱስትሪዎች አማካይ የማምረት አቅማቸውን ከ42 ነጥብ 6 በመቶ ወደ 85 በመቶ እንዲደርስ ታቅዶ ወደ ስራ መገባቱንም አመላክተዋል።

እንደ ምክትል ከንቲባው ገለጻ፤ ተኪ ምርቶችን በማምረት የውጭ ምንዛሪ ገቢን ማሳደግ የከተማ አስተዳደሩ አንድ ስትራቴጂክ እቅድ ነው፡፡ ተኪ ምርት አምራች ኢንዱስትሪዎቸ እንዲሰፉ በማድረግ ከነበሩበት 418 ወደ 1 ሺህ 226 ለማሳደግ ታቅዷል። ወደ ውጭ የሚላከው የኢንዱስትሪ ምርት ከነበረበት 133 ወደ 381 በማድረስ የውጭ ምንዛሪ ግኝቱን ከነበረበት 1 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዶላር ወደ 2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር የማሳደግ እቅድ ተይዞ እየተሰራ ነው።

የኢንተርፕርይዝ ኃላፊዎች እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትም በመድረኩ ላይ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ የከተማው አስተዳደርም ለቀረቡ ጥያቄዎች በወቅቱ መልስ ሰጥቷል፤ አስተዳደሩ እንደ መስሪያ ቦታ ያሉ የአንዳንድ ኢንተርፕራይዞችን ጥያቄዎች በአፋጣኝ የመለሰበት ሁኔታም ታይቷል፡ ፡ በእዚህ ጥያቄያቸው ከተመለሰላቸው መካከል በንቃናቄው ተሳታፊዎች ጉብኝት የተደረገበት ዘናጭ ጋርመነት አንዱ ነው።

በአዲስ አበባ ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ የሚገኘው ይህ ጋርመንት፣ በምርቶቹ ከውጭ የሚገቡ አልባሳትን ለመተካት እየሰራ ይገኛል። ለበርካታ ወጣቶች የስራ እድል በመፍጠር የእለት ጉርስ ሆኖላቸዋል።

ወጣት አብረሃም ተስፋዬም በጋርመንቱ የስራ እድል ካገኙ ወጣቶቸ አንዱ ነው። በጋርመንቱ መስራት ከጀመረ ሁለት አመታተን አስቆጥሯል፡፡ ወጣቱ የሙያ ስልጠና አግኝቶ ወደ ስራ መሰማራቱ ሌላ የስራ አማራጭ እንደሆነለት ነው የሚናገረው። አብረሃም ዘናጭ ጋርመንት ከመቀጠሩ በፊት እየተማረ በትርፍ ጊዜው ደግሞ ጂብሰም እየሰራ ያገኘውን በመቆጠብ ለመለወጥ ጥረት ያደርግ ነበር፤ የኮንስትራክሽን ስራዎች መቀዛቀዝ ግን በእዚህ ስራው እንደ ፊቱ መቀጠል አላስቻለውም፤ ስራ አጣ፤ ይሄኔ ታዲያ አስቀድሞ ወደ ጋርመንቱ የመጡ ጓደኞቹ ስለ ድርጅቱ መረጃ ሰጥተው ድርጅቱን እንዲቀላቀል አድርገውታል።

ከዚያም የልብስ ስፌት ስልጠና ይወስዳል፤ በየደረጃው እየሰለጠነ ውጤታማ ስራ መስራት የጀመረው ወጣት አብረሃም፣ ለነገ የተሻለ ሙያ ኖሮት የራሱን ስራ ለመፍጠር እያቀደ ስራውን በትጋት እያከናወነ መሆኑን ይገልጻል። በጋርመንቱ ደመወዝ እንደየደረጃው እንደሚከፈል ጠቅሶ፣ ሰራተኞቹ የሙያ



**አቶ ተስፋዬ አባቴነህ**

ብቃታቸው እየጨመረ ሲሄድ ክፍያውም እየተጨመረለት እንደሚሰራ ተናግሯል።

ሌላዋ ወጣት ብርቱኳን ጌታቸው ከሶስት አመት በፊት ጀምራ በጋርመንቱ መስራት መጀመሯን ትናገራለች። በማታው የትምህርት መርሀ ግብር እየተማረች ቀን ቀን ለመስራት እያሰበች ባለችበት ወቅት ነው የቀን ስራ ስትፈለግ ጋርመንቱ ምንም ሙያ የሌላቸውን ወጣቶች አስልጥኖ ወደ ስራ የሚያስገባ መሆኑን ትሰማለች። የ23 አመቷ ወጣት ብርቱኳን በማታው የትምህርት መርሃ ግብር የቀለም ትምህርቷን፣ በቀን ደግሞ የሙያ ክህሎቷን አዳብራ ልብስ ሰፊ ለመሆን መቻሏን ታስረዳለች። አሁን ሁለት ሺ አምስት መቶ ብር እየተከፋላት ትምህርቷንና ስራዋን ጎን ለጎን ታስኬዳለች።

እንደ ወጣት አብረሃምና እንደ ወጣት ብርቱኳን አይነት በርካታ ስራ አጥ ወጣቶችን በአንድ አሰባስቦ የስራ እድል የፈጠረላቸው ጋርመንት ዘናጭ ጋርመንት ባለቤትና ስራ አስኪያጅ አቶ ተስፋዬ አባቴነህ ይባላሉ። በመካከለኛ እድሜ ክልል የሚገኙት እኚህ ሰው ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀው ቅጥርን ከመጠበቅ የራስን ስራ ፈጥሮ መንቀሳቀስ በሚል ሀሳብ ከጓደኛቸው ጋር መከረው አንድ የስራ ዘርፍ ላይ ለመሰማራት ተስማሙ።

ከሀረማያ ዩኒቨርሲቲ በኮኦፖሬቲቭ አካውንቲንግ የትምህርት ዘርፍ የተመረቁት እኚህ ሰው በወቅቱ ዲግሪ ኖሯቸው ስራ ያጡ ወጣቶችን በማደራጀት ወደ ስራ እንዲገቡ የማድረግ አሰራር ስለነበር በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስድስት ተደራጅተው ለመስራት ተዘጋጁ። በስራ ጉጉት ላይ ጥቂት የቤተሰብ ድጋፍ ተዳመረ፡፡ የየካ ወረዳ አንድ ደግሞ የመስሪያ ቦታ ፈቀደላቸው፡፡ እነዚህ ወጣቶች በወጣትነት ሀይል ስራ ለመጀመር መንገዱ እየቀናላቸው መጣ፡፡ ከያዙት በተጨማሪ ከአዲስ ብደርና ቁጠባ በተገኘ ብድር 20 የስፌት ማሽኖች በመግዛት ቦታውን ለስራ ምቹ አደረጉት።

በ2010 ዓ.ም 12 ሰራተኞችን ይዞ ስራ የጀመረው ዘናጭ ጋርመንት፣ ሰራተኞቹ ከቴክኒክና ሙያ ተቋም በልብስ ስፌት የተመረቁ ናቸው፡፡ ስራው ሲጀመር እነሱ ያገኙትን የስራ እድል ለሌሎች ለማካፈል በማሰብ ከአዲስ ምሩቆች ጋር ስራ ይጀመራሉ።

መነሻ ካፒታሉ ሰማኒያ ሺ ብር ከቤተሰብ የተገኘ ብድር ሲሆን፣ ከአዲስ ብድርና ቁጠባ ለማሽን መግዣ 430 ሺ ብር ብድር ወስደው ማሽኖቹን ይገዛሉ። በቅድሚያ መርካቶ ውስጥ ያሉ ሱቆች የተቀበሉትን የስፌት ትእዛዘ በመቀበል ጨርቅ ከነጋዴዎቹ ጉልበት ደግሞ ከጋርመንቱ በማድረግ እየሰሩ የእጅ ዋጋ እየተከፈላቸው መሰራት ይጀምራሉ።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ስራ አብረው ከጀመሩት ጓደኛቸው ጋር ቢለያዩም አቶ ተስፋዬ ስራውን አጠናክሮ በመቀጠል ማሳደግ ጀመሩ። ለአንድ አመት ያህል በእጅ ዋጋ ሲሰራ የቆየው ጋርመንቱ ከአመት በኋላ ሰራተኞቹን ወደ አርባ አሳድጎ የራሱን ምርት ማምረት ውስጥ ገባ። የሰራተኞች ብዛት በየጊዜው ቢቀያየርም፣ አሁን በወቅታዊነት በጋርመንቱ ከአንድ መቶ አስራ አራት በላይ ሰራተኞች በጋርመንቱ ይሰራሉ።

በኢንዱስትሪ ፓርኮች የተመረቱ ጣቃ ጨርቆችን በመጠቀም ማሊያዎችን፤ ቲሸርቶችን፤ ፓካውቶች፤





ፎቶ ሀዲስ አብርሃ

**ጋርመንቱ በአሁኑ ወቅት ከ 114 በላይ ሰራተኞች አሉት**

የወንዶች የውስጥ ሱሪዎችን በምርጥ አጨራረስ በመስፋት ከውጭ ከሚገቡት ጋር ተወዳዳሪ ለመሆን የሚችል ምርት እያመረተ መሆኑን አቶ ተስፋዬ ያብራራሉ። ብትን ጨርቁም በአገር ውስጥ የሚመረት በመሆኑ ምንም አይነት የውጭ ምንዛሪ ሳይፈልገ ስራውን ማካሄድ የሚችል ጋርመንት በመሆን ለአገር ኢኮኖሚ የበኩሉን አስተዋፅኦ እያደረገ የሚገኝ መሆኑን አስረድተዋል።

ጋርመንቱ አሁን እያመረተ ካለው በእጥፍ የማምረት አቅም እንዳለው የሚናገሩት አቶ ተስፋዬ የመስሪያ ቦታ ጥበት፤ ስራ ለማስፋፋት የገንዘብ አቅም ማነስ፤ ለብድር የሚጠየቀው የዋስትና ንብረት ከአቅም ጋር ያልተመጣጠነ መሆኑን እንደ ችግር ይጠቅሳሉ። በቅርቡ በተካሄደው «ኢትዮጵያ ታምርት» በሚል የንቀናቄ መድረክ ላይ እነዚህን ችግሮች ማንሳታቸውንና ፈጣን ምላሽ እንዳገኙም አስረድተዋል።

አሁን ከሚሰሩበት ሺድ ተጨማሪ ስለተሰጣቸው የማምረቻ ቦታ ጥበቱ ተፈትቶላቸዋል፡፡ የቦታ እጥረቱ መፈታቱ ብዙ ችግሮችን እንደፈታላቸው አቶ ተስፋዬ ይናገራሉ፡፡ ማሽኖችንም በማስመጣትና አሁን ካለው የሰው ሀይል እጥፍ ለመቅጠር እንዲሁም በምርት በኩል እጥፍ ለማምረት የሚያስችል ቁመና ላይ መድረሱን ይገልጻሉ።

አሁን ባለው አቅም በቀን እስከ ሶስት ሺ ልብስ የሚሰራ መሆኑን ገልፀው፣ በቀን ከሚመረተው ልብስ እስከ አስራ አምስት ሺ ብር ገቢ እንደሚገኝ አስረድተዋል። የማስፋፊያ ቦታ ሳይጨመር በቤቱ ውስጥ በአጠቃለይ 100 ማሽኖች ይዘው የሚሰሩ እንደነበር ጠቅሰው፣ ከገበያ ፍላጎቱ አንፃር ምንም እየተሰራ አለመሆኑን ነው ያስታወቁት።

እንደ ስራ አስኪያጁ ገለጻ፤ በጥቂት ጥሪት የተነሳው ይህ ጋርመንት አሁን 25 ሚሊየን አካባቢ የተመዘገበ ካፒታል ይዞ ይንቀሳቀሳል። ማስፋፊያው ተጠናቆ አቅሙ በእጥፍ ሲያደግ ደግሞ ለበርካቶች የስራ እድል ከመፍጠሩ ባሻገር ተኪ ምርቶችን በማምረት እነዚህን ልብሶች ለማምጣት የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ለማስቀረት መቻሉን ያስረዳሉ።

በጥቂቱ ተነስተው ለበርካቶች የስራ እድል መፍጠር የቻሉ፤ ለራሳቸው ሀብት አፈርተው አገርን ከድህነት ለመላቀቅ የሚያስችል ስራ የሚሰሩ፤ የአገርን የውጭ ምንዛሪ አገር ውስጥ ለማስቀረት የሚታተሩ በርካታ አነስተኛ መካከለኛና፤ ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን አገሪቱ አፍርታለች፡፡ እነዚህ ኢንዱስትሪዎች አሉብን የሚሏቸውን ችግሮች በመንቀስ ድጋፍ ከተደረገላቸው የበለጠ ለውጥ የማይመጣበት ምክንያት አለመኖሩንም አቶ ተስፋዬ ያብራራሉ።

በንቀናቄ መድረኩ ላይ የተለያዩ ሀሳቦች መነሳታቸውንና በዋንኛነት የፋይናንስ እጥረት ስራቸውን አስፋፍተው እንዳይሰሩ እንዳደረጋቸው አቶ ተስፋዬ አስታውሰው፣ ለብድሮች መያዣ ተብለው የሚጠየቁት ንብረት ከአቅም በላይ የሆነ የተለያዩ የቢሮክራሲ መስመሮች ስራውን በተቃና መልክ እንዳይሄድ እንዳደረገው ተናግረዋል።

የሀይል አቅርቦት ችግር፤ ሰፊ የማምረቻ ቦታ ማጣት፤ ስልጠናዎችን የሚፈለጉ አምራቾች የክህሎት ስልጠና አለማግኘታቸው፤ የውጭ ምንዛሪ እጥረትና ሌሎችም በመድረኩ የተነሱ ሲሆን፣ ለዚህም ከመድረኩና የውይይቱ ታዳሚ የነበሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ ለተግባራዊነቱ መትጋት ግድ ይላል።

ከዘናጭ ጋርመንት ተሞክሮ እንደተረዳነውም እንዲህ አይነት ኢትዮጵያ ታምርት አይነት ንቅናቄዎች የአምራቾች ችግሮች አዳምጦ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ወሳኝ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ አስፈፃሚውም ሆነ አምራቹ የሚያከናውኑት ተግባር ለአገር ኢኮኖሚ ጠቀሜታው የላቀ ነው። አገር በሌሎች አገራት ምርቶችና ኢኮኖሚ ላይ ከመንጠልጠል የሚያወጣትን ተግባር ለማከናወን አምራቾችን መደገፍ የግድ መሆኑን በመረዳት መሰል እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው ይቀጥሉ በሚል መልእክታችን የዛሬውን አበቃን።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

## ጎሜ

# እንደጊዜው...

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

አለቃ ገብረ ሃና ቀልድ አዋቂ ስለመሆናቸው አገር ያወቀው ፀሀይ የሞቀው ስለመሆኑ ለእናንተ አላወጋም። አለቃ በጣም አጭር ሰው ናቸው ይባላል። ሚስታቸው ወይዘሮ ማዘንጊያሽ ደግሞ ሲበዛ ረጅም ናቸው። መንገድ ውለው ወደቤታቸው ሲመለሱ ወይዘሮ ማዘንጊያሽ ሰማዩን አይተው አለቃ ዝናብ ሊዘንብ ነው መሰለኝ ይሏቸዋል አጭር በመሆናቸውና በነገር ሊወርፏቸው ፈልገው። ከዚያ አለቃ ከኋላቸው ኩስ ኩስ እያሉ ሲመልሱላቸው! «እኔ ምን አውቃለሁ ለሰማዩ ቅርቡ አንቺ ነሽ» አሏቸው ይባላል። አንጀት አርስ መልስ ይልኸል ይህ ነው!

ወዳጄ ምን መሰለህ! አንዳንድ ጊዜ ለማን ምን እየተናገርን እንደሆነ ማወቅ ጥሩ ነው። አንዳንድ ጊዜ ዝም ብለህ ማየት የሌለብህን አትመልከት። እንበልና የሆነ ጉዳይ ገጥሞህ ወይንም የሆነ ነገር ለማስፈፀም የሆነ ቢሮ ሄደህ እንበል። ታዲያ ጉዳይህ ይህ ሆኖ ሳለ የፀሐፊዋን ሁኔታ በጥልቀት መመልከቱና ያን ያክል ስለ እርሷ መመራመሩ ጅልነት ሊሆን ይችላል። የቢሮው ውበት፣ ከፀሐፊዋ ጠረጴዛ ላይ የተደረደረው የባለጉዳይ ይሁን ምንነቱ የማይታወቅ የወረቀት ተራራ፣ በፀሐፊዋ ቢሮ ውስጥ የተደረደሩ ስልኮች ብዛት መቁጠር ምንም አይጠቅምህም። በእርግጥ! ይጠቅመኛል የሚል ሰው ካለ መብቱ ነው።

እሺ አሁን የፀሐፊዋን መቀመጫ ማየት ጥቅሙ ምንድን ነው። በቃ ይህ መቀመጫ ማለቴ ወንበሩ ይገባት ይሆናል ወይንም አለቃዋ ስለወደደው ሊሆን ይችላል። በቃ! አለቃ ከወደደው ወደደው ነው ሌላ ምን አለ? ይልቅስ ጉዳይህ ላይ ብቻ በማተኮር አጀንዳህን አጠናቀህ እግር ወደመራህ ሂድ!

በነገራችን ላይ ስለ ፀሐፊዎች ካነሳን አይቀር የሆነ ነገር አልታዘባችሁም። ለምሳሌ በቁመናቸው መልከ መልካም፣ ዓይነ ግቡ፣ ሞንዳላ ዓይነት ተክለ ቁመና የተላበሱ ሲሆኑ በባህሪያቸው ወጣ ያሉ ለምሳሌ ቆጣ ቆጣ የሚሉ ወይንም በጣም ተግባቢና አስተዋይ፣ ለምሳሌ በሁሉም ነገር ውሳኔ ሰጪ ነን የሚሉ ወይንም የማይመለከታቸውን ሁሉ የሚጠይቁ፣ ወንድ መሆንህ እየተመለከቱ ፆታህ ምንድን ነው ብለው የሚጠይቁህ፤ ትዕግስትህን የሚፈታተኑህ ወይንም የሚፈታተኑሽ። አሁን አንድን ባለ ጉዳይ ጾታ መጠየቅ ከኃላፊና ከፀሐፊዋ ጋር ምን ያገናኛቸዋል? ለነገሩ ሊገናኝ ይችል ይሆናል። ለምሳሌ በቃ ብዙ ብዙ ነገር ላይ ለምሳሌ የሚያስብሉ ነገሮችን የተላበሱ ሆነው አላገኛችሁም?

በነገራችን ላይ መልከ መልካም፣ ተግባቢ ብቻ መሰል ባህሪ የሚስተዋልባቸው ፀሐፊዎች ጥቅማ ጥቅማቸው ምንድን ነው ብዬ አስባለሁ። ለረጅም ጊዜ ቢሮ ውስጥ ናቸው። ወጭ ወራጁ ሁሉ በእነርሱ ዘንዳ ካላለፈ የተሰራም አይመስላቸውም። ይህን ሁሉ የሚከታተሉት ጥቅማጥቅማቸው ምንድን ነው ብዬ ሳስብ ግን ግራ ይገባኛል። ለነገሩ እንደዚህ እኮ አይጠየቅም። ዝም ብሎ ማለፍ አይበጅም። ለዚያም በትይዩ ሳይሆን በስር ማለፍ፤ ዝቅ ብሎ።

ከማህበራዊ ሚዲያዎች ያገኙሁት አንድ የእብዶች ቀልድ ትዝ አለኝ። «አማኑኤል ሆስፒታል አንድ የአዕምሮ ዶክተር እብዶች ወደ ውጭ እየወጡ ያስቸግሩትና በመውጫው በር ወለሉ ላይ መስመር ያሰምርና «ከዚህ በኋላ ማንም ከዚህ መስመር እንዳያልፍ» ይላቸዋል። ትንሽ ቆይቶ ሲመጣ ወለሉ ላይ እነዚህ አዕምሮ ህመም ያለባቸው ታካሚዎች ሲንፏቀቁ ያያቸውና «ምን እየሠራችሁ ነው?» ሲላቸው አንዱ ተነሳና «በሥር ልናልፍ ነው» ብሎ ይመልሳል። መሬት ላይ በቀለም ከተሰመረው መስመር ሥር መሆኑ ነው። አያችሁ አንዳንዴ ማለፍ ጥሩ ነው። መጠየቅ

> **ወዳጄ! ቀልድህን በልኩ አድርገው፤ የምታሞኘው ሰው ሁሉ ሞኝ ስለሆነ ሳይሆን ማለፍን ለነገሮች እንደመተሳለፊያ አድርጎ ስለሚያስብ፤ እርሱ ከአንተ የተሻለ መሆኑን ስለሚያውቅ ነው። ማንን እየሸወድክ እንደሆነ እወቅ። ፀሐፊዋን ገላምጠህ ከኃላፊው ዘንድ ስትደርስ ምንም እንዳልተፈጠረ አድርገህ ጉዳይህን ልታወራ ትችላለህ**

የማይገባንን መጠየቅ፣ ማወቅ የሌለብን ለማወቅ መጨነቅ፣ የማይፈቀደውን ለማስፈቀድ መራኮት ምን ሊበጅ! በቃ ማለፍ ነው። ሌላው ቀርቶ በማይቻል ሁኔታም ቢሆን እንደ ዕብዶቹ ከመስመሩ ስር ለማለፍ መመኮር።

ማለፍ የሚለውን ካነሳን አይቀር ትዕግስተኛ መሆን፤ ማለፍ መልካም ነው። ወደ ኃላፊ ለማለፍ ወይንም ለመሄድ ፀሐፊዋ ማለፍ አለብህ። እንዴት ብሎ መጠየቅ ምት ቢሆንም ለዚህ ብዙ መልስ መስጠት አልችልም። ብዙ የማለፍና የመተላለፍ ህጎች በመኖራቸው እንዲያው ማለፍ መልካም ነው በሚለው ብንረዳዳ ሸጋ ነው።

እንዲያውም ይህን ሃሳብ አላልፈውም። ማለፍ ማለት መተው ነውን፤ አይደለም። ማለፍ ማለት በተበላሹ ዛሬዎች ውስጥ የተበላሸ ነገን ላለመፍጠር መታገስ ማለት ነው። ማለፍ ማለት አለመቻል ሲሆን እየቻሉም ቢሆን አለመቻል ነው። መሰንዘር ስንችል መሰብሰብን፤ መናገር ስንችል አለመናገርን፣ መቆጣት ስንችል መታገስ እና ብቻ በብዙ መቻሎች ውስጥ ምንም አለመቻል ነው።

ይህ ማለት ግን እልም ያለ ጅልነት አለመሆኑን ልብ ይሏል!፡ አንዳንድ ጊዜ እኛ ብቻ ብልጥ የሆንን የሚመስለን፣ እኛ ብቻ የመራን፣ እኛ ብቻ የገነባን፣ እኛ ብቻ የተማርን፣ እኛ ብቻ የተሰማን፣ እኛ ብቻ ያገኘን፣ የእኛ ብቻ የጻፍን የሚመስለን አያሌዎች ነን፤ ያው ስለፀሐፊ አንስቼ የለ!

አንዳንዴ ብልጠታችንና ማወቃችን በወጉ መያዝ ጥሩ ነው። ብልጥ እኛ ብቻ የሚመስለን ግን ደግሞ ምንም የሆንን ብዙዎች ነን። እኔ ብቻ ብልጥ ለሚሉ ሰዎች አንድ ተረት ትዝ አለኝ።

ከዕለታት አንድ ቀን እንዲህም ሆነ፤ የደብሩ አለቃ ዛፍ ቆራጮችን ይኮናተሩና ሥራው እየተካሄደ ሳለ የገብርኤል ዕለት ከቆራጮቹ አንዱ በጣም ረጅም ዛፍ ላይ ወጥቶ ቅርንጫፍ ሲመለምል፤ ከፉ ነፋስ ይነሳና ያን ረጅም ዛፍ እንደጭራሮ ያወናጭፈው ጀመር። የዚህ ሁኔታ መፈጠር እጅግ በጣም ያስደነገጠውና ያስፈራው ቆራጭ፤ «ወይኔ ሲያቀብጠኝ በገብርኤል ዕለት! ለዚያውም በደብር ውስጥ። ገብርኤል ተቆጥቶ ሊገለኝ ነው» እያለ ካለቃቀሰ በኋላ «እንዲያው ቅዱስ ገብርኤል! የዛሬን ያወጣኸኝ እንደሁ አሥር ብር አገባልሃለሁ» ብሎ ይሳላል። ወዲያው ስለቱን ሲጨርስ ነፋሱ ጸጥ ረጭ ይልለትና ከዚያ ዛፍ ላይ እየተሽቀዳደመ ይወርዳል። ሁለት እግሮቹ መሬት ላይ ሲቆሙ የአሥር ብሩ ነገር ይከነክነውና «ኤጭ! እኔ ሥርቼ በላቤ ወዝ ነው የማድረው፤ ገብርኤልም ሠርቶ ይብላ» ብሎ ስለቱን ላለማግባት ወሰነ። ትዝ ቢለው ለካ መፋሱን እዚያ ረጅም ዛፍ ላይ ትቶት ወርዶ ኖሯል። ፊቱን ወደሰማይ ዞር አድርጎ፤ የርብድብድ ፈገግታ እያሳየ «ምነው ገብርኤል ቀልድ አታውቅም እንዴ!» አለ ይላሉ።

ወዳጄ! ቀልድህን በልኩ አድርገው፤ የምታሞኘው ሰው ሁሉ ሞኝ ስለሆነ ሳይሆን ማለፍን ለነገሮች እንደመተላለፊያ አድርጎ ስለሚያስብ፤ እርሱ ከአንተ የተሻለ መሆኑን ስለሚያውቅ ነው። ማንን እየሸወድክ እንደሆነ እወቅ። ፀሐፊዋን ገላምጠህ ከኃላፊው ዘንድ ስትደርስ ምንም እንዳልተፈጠረ አድርገህ ጉዳይህን ልታወራ ትችላለህ። ወዳጄ አትሞኝ አንተ ከኃላፊው ዘንድ ከመድረስ በፊት እንኳስ የተናገርከው ያሰብከው ሁሉ ቀድሞ ከእርሱ ዘንድ ይደርሳል። ያወቅህ ይመስለህል፤ ግን ተሸውደሃል። በምትናገራቸው ነገሮች ሁሉ ምንነትህ ይገለፃል። ተረጋጋ! በማለፍ ውስጥ መተላለፍ መኖሩን አትርሳ። ዓለም ዝብርቅርቅ ናት። ከፀሐፊ እስከ አለቃዋ ድረስ ረጅም ጉዞ ሰፊ ልዩነት አለ፤ ዓለም አሽቃባጭ ናት የምንላት ነገር አለች ብሽቅ ሲለን።

ይልቅስ እጅና እግር በሌለው ነገር ሰው ለማሳመን አትሄድ ከንቱ ድካም ይሆንብሃልና። በነገራችን ላይ እጅና እግር ስል ትዝ ያለኝ ነገር ቢኖር ዘንድሮ በእግር ብቻ ሳይሆን በእጅህም መሄድ አለብህ የሚሉት ጣጣ እየመጣ ነው። ባለጉዳይ ሆነህ ፀሐፊዋም ከጥሩ መቀመጫዋ ብድግ ብላ ፈገግታ የተሞላበት የሞቀ ሰላምታ ሰጥታህ አለቃው ዘንድ ደረስክ እንበል። ደስ ይላል! ጉዳዩ በቅፅበት ሊሳካ ነው ብለህ አሰፍስሃል።

ኃላፊው ከተመቻቸው ወንበር ላይ ሆኖ እያዳመጠህ ነው፤ ድንቄም ማዳመጥ!፡ ጉዳይህን ዘርዝረህ አስረድተሃል፤ የሚጠበቅብህን መስፈርት በሙሉ አሟልተሃል። አሁን ግን ትንሽ መጠበቅ አለብህ ትባላለህ። ዛሬ የምትጨረሰውን ጉዳይ ነገ በጠዋት ብቅ ብለህ እንዲፈፀምልህ ይነገርህና እጅ ነስተህ፤ ከወገብህ ጎብጠህ ትወጣለህ። በነጋታው ማለዳ እንደተለመደው ከባለጉዳይ ሁሉ ቀድመህ ተገኝተሃል።

ወዳጄ አሁን ግን ትንሽ ጠብቅ ትባላለህ። መጀመሪያ መጥተህ መጨረሻ ትገባለህ። የሌሎች ጉዳይ ፈር ሲበጅለት አንተ በአንድ አዳር ጉዳይህ እንደ አዲስ ውስብስብ ሆኖ ታገኛለህ። ይፈፀምልሃል የተባለው ጉዳይ ሊሳካልህ ቀርቶ፤ የሕይወት ፍፃሜ ላይ የደረስክ እስኪመስልህ ድረስ እንደ አዲስ ግራ ትጋባለህ።

ቅድም እንደነገርኩህ ዘንድሮ በእግር ብቻ መሄድ አያወጣም። በእጅ መሄድ የሚባል ነገር አለ። እንዴት በእጅ እሄዳለሁ አይባልም። ይኬዳል እንጂ ለዚያውም መላ ሰውነትህን እስከሚያሳክክህ፤ እንደ ኪስ ሰውነትህ ጉርጉድ እስኪል ድረስ። ደግሞ ኪስ እና ባለጉዳይ ምን አገናኛቸው አትበል። የማይገናኙ ብዙ የተገናኙ ነገሮች አሉ። እሺ ኃላፊ እና ፀሐፊዋን ምን አገናኛቸው፤ አንተ እና ፀሐፊዋ ምን አገናችሁ፤ አንተና ኃላፊውን ምን አገናኛችሁ፤ አንተ እና ጉዳይህን ማን አስተሳሰራችሁ፤ ጭራሽ የማይታሰበውን አታስብ ወዳጄ።

አየህ ትኩረትህ በሚጠቅምህ ነገር ላይ አድርግ የምልህ ለዚህ ነው። የፀሐፊዋን መቀመጫ (ተሽከርካሪ ወንበር!) ማማር ሳይሆን፤ አካሄድህን አሳምር ብሎ የመከረህን ጓደኛ ምክር አትርሳው። እንደጊዜው በእግርህ ብቻ ሳይሆን በእጅህም ሂድ የሚለው ምክሩ በጣም ላትስማማበት ትችላለህ። ግን እኮ እየሆነ ያለው ይህ ነው። እንደ ዛፍ ቆራጩ የማይታለለውን ለማታለል ከምትሞክር ዝም በል። አለቃ ገብረሃናን የመሰሉ ሰዎች ሲገጥሙህና ምላሽ መስጠት በማትችልበት ሁኔታ ውስጥ ስትሆን ዝም በል፤ ነገም ሌላ ነው። በቃ ታገስ ዝም በል! ዝም አይነቅዝም ይባል የለ!

# የዘመን ጥበብ

## የጉማ ሽልማት እና የሚፈጥረው የፊልም መነቃቃት

ዋለልኝ አየለ

በየዓመቱ የሚካሄደው ጉማ የፊልም ሽልማት ከተጀመረ እነሆ ዘንድሮ 8ኛ ዙር ላይ ደርሷል። በዛሬው ዕለትም የ8ኛ ዙር የጉማ ፊልም አሸናፊዎች ይታወቃሉ።

ጉማ የፊልም ሽልማት የፊልም መነቃቃት ይፈጥራል፤ ፈጥሯልም። ምንም እንኳን የሽልማቱ ትኩረት በተሰሩ ፊልሞች ላይ ቢሆንም፤ ወደፊት በሚሰሩ ፊልሞች ላይ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፤ መነቃቃትን ይፈጥራል።

የፊልም መነቃቃት ይፈጥራል ሲባል፤ ዕጩዎች ከቀረቡበት ጊዜ ጀምሮ ስለፊልም ይወራል። ስለተዋናዮች ብቃት ይወራል፤ ስለፊልሞች ይዘት ይወራል። የትኛው ፊልም ይሸለም ይሆን በሚል ፊልሞችን የመዳሰስ ሥራ ይሰራል። በተለይም በዕጩነት የቀረቡ ፊልሞች ስም ሲዘረዘር፤ ፊልሞችን ያላዩ ሰዎች አፈላልገው እንዲያዩት ሊገፋፋ ይችላል።

የተዋናዮች ማንነት ይታወቃል። በተለይም ወጣት ተዋናዮች ሥራዎቻቸውና ብቃታቸው እንዲታይላቸው እድል ይሰጣል። ጉማ የፊልም ሽልማት እንቅስቃሴ ከሚጀመርበት ሰሞን ጀምሮ በመገናኛ ብዙኃንም ሆነ በመድረኮች ስለፊልም ይወራል፣ ስለዕጩ ተዋናዮችና ሥራዎቻቸው ይቃኛል። በዚህ ሁሉ ውስጥ የፊልም መነቃቃት እየተፈጠረ ነው ማለት ነው። በአዘቦት ስለፊልም የማይሰሩ መገናኛ ብዙኃን ሁሉ በዚህ ሰሞን ትኩረታቸውን ወደ ፊልሙ ያዞራሉ። እግረ መንገድም አንዳንድ ፊልሞች ላይ ዳሰሳዎች ይሰራሉ ማለት ነው።

በሌላ በኩል ጉማ የፊልም ሽልማት የተለያዩ ዘርፎች ስላሉት፤ የተለያዩ የፊልም ሙያዊ መመዘኛዎችን ወደ ፊልሙ ዘርፍ የሚገቡ ሰዎች ይማሩበታል ማለት ነው። ፊልም ሲባል ብዙዎቻችን የምናውቀው ያለቀለትን ሥራ ነው። ዘርፎቹ ተዘርዝረው ስናየው ግን ከጀርባው ብዙ ቴክኒካል ነገሮች እንዳሉ ይታወቃል። ይዘቱን ብቻ ሳይሆን ከፊልሞች ጀርባ ተደብቀው ያሉ ከማጀቢያ ሙዚቃው ጀምሮ የሜካፕ፣ የመብራት ወዘተ ባለሙያዎችን ሁሉ ብቃትና ልፋት እንዲገለጥ ያደርጋል። እነዚህን የፊልም ጥበቦች ብዙዎቻችን ልብ ስለማንላቸው በጉማ የፊልም ሽልማት ምክንያት ትኩረት ያገኛሉ።

ዛሬ የሚደረገውን 8ኛው ጉማ የፊልም ሽልማት ምክንያት በማድረግ ስለፊልም ማውራት ተገቢ ነው። በዛሬው ፕሮግራም እነማን ተሸላሚ እንደሚሆኑ ስለማናውቅ ባለፉት ዓመታት የነበሩትን ፊልሞችና ተሸላሚዎች እናስታውስ። ሁነቶች የፈጠሩትን የፊልም አብዮትም በነካ እጃችን እንቃኝ።

ፊልም በተለያዩ ዘርፎች ቢከፈልም፤ የሰውን ልጅ የአሁኑን የትላንቱንና የነገውን ሁኔታውን የሚያስተላልፍበት መገናኛ መንገድ ነው። የፊልም ሥራዎቻቸው ባደጉት በትላልቆቹ ዓለማት ደግሞ ያሉበትን ሉዓላዊነት ማንፀባረቂያ፣ ያላደጉትን አገራት ማስፈራርያ እና መማረኪያ ንብረታቸው ነው። ራሱን የቻለ ግዙፍ የኢንዱስትሪ ዘርፍም ነው።

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ ግን፤ ኢትዮጵያና ፊልም ያላቸው ትውውቅ ከአንድ ክፍለ ዘመን የተሻገረ ቢሆንም የዘመናዊ ፊልም ታሪኳ ግን ከሃያ ዓመታት ያልዘለለ ሆኖ እናገኘዋለን።

የኢትዮጵያ ፊልም እንደ ኢንዱስትሪ መታየት ጀምሮ በብዙ ውጣውረዶች አልፎ በሲኒማ ቤቶች ደረጃ መታየት የጀመረው ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ነው። እንደ ጉዲፈቻ፣ የበረፌዶ ዘመን፣ ስላንቺ፣ የወንዶች ጉዳይና የመሳሰሉት ፊልሞች የኢትዮጵያ ዘመናዊ የፊልም ታሪኳ ውስጥ በምሳሌነት ከሚጠቀሱት ጥቂቶቹ ናቸው።

እነዚህን ፊልሞቻችንን ይዘን ጉማ የፊልም ሽልማት ተጀመረ። ከሃምሳ ምናምን ዓመታት በፊት በሚሼል ፓፓታኪስ የተሠራው እና በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ባለቀለም ፊልም በሆነው ‹‹ጉማ›› ፊልም መጠሪያውን ያደረገው ጉማ የተሰኘው ሽልማት ነው ዛሬ ላይ ስለፊልሞች በሰፊው እንድናወራ ያደረገን።

የአዘጋጆቹ ትጋትና ለፊልም ኢንደስትሪው እያበረከቱት ያለውን አስተዋፅዖ ማንም ወደ ፊልሙ ተጠግቶ የማያውቅ እንግዳ ሰውም ሊመሰክረው የሚችለው ጉዳይ ነው። የተለያዩ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ፊልሞችን እየያዘ የሚመጣው ጉማ የፊልም ሽልማት በየዓመቱ ደመቅ ባለመልኩ ነው የሚከናወነው።

በነገራችን ላይ ጉማ የፊልም ሽልማት በ2012 ዓ.ም የተከሰተውን የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት በማድረግ አልተካሄደም ነበር። ባለፈው ዓመት ነው እንደገና በደማቁ የተጀመረው። የባለፈው ዓመት 7ኛው የጉማ ፊልም ሽልማት ብዙ አነጋጋሪ ክስተቶች የታዩበት ነበር።

በኢትዮ ፊልም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት የሚዘጋጀው ጉማ ፊልም ሽልማት ጥሩ ብቃት ላሳዩ ፊልሞች እና አርቲስቶችን ክብርና እውቅና መስጠት ዓላማው እንዳደረገ አዘጋጆች በተለያየ ጊዜ ተናግረዋል።




**የፊልም ኢንዱስትሪው እንዲያድግና፤ በኢኮኖሚው ውጤታማ እንዲሆን ሁሉም የተቻለውን ጥረት እንዲያደርግ ያነሳሳል። ሆኖም ግን የመንግሥትም ድጋፍ መደረግ አለበት። ምክንያቱም ፊልሞች የኢትዮጵያን ባህል በማስተዋወቁም ረገድ ሆነ ዓመታዊ ገቢን ከፍ እንዲል በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል**

በባለፈው ዓመት ሰባተኛው የሽልማት መርሃ ግብር ላይ 45 ፊልሞች የተመዘገቡ ሲሆን ከእነዚያ ውስጥ 15 ፊልሞች በተለያዩ 16 ዘርፎች ታጭተው ነበር። ‹‹እንሳሮ›› የተሰኘው የምስጋና አጥናፉ ፊልም በ13 ዘርፎች ታጭቶም ነበር።

የፍቅር ጥግ በ11፣ ማንያዘዋል በ11፣ ስንብት በ10፣ ከርቤ በ8፣ ምን አለሽ በ8፣ ሱማሌው ቫንዳም በ6 ዘርፎች ታጭተው ነበር። በዳይሬክቲንግ፣ በሲኒማቶግራፊ፣ በትወና እና በሌሎችም በአጠቃላይ 18 ዘርፎች ውድድር ተካሄዷል።

በምርጥ አጭር ፊልም ቀብድ፣ በምርጥ የፊልም ጽሑፍ እንዲሁም በምርጥ ፊልም ቁራኛዬ አሸናፊ ሲሆን በምርጥ ሲኒማቶግራፊ እንዲሁም ኤዲቲንግ ደግሞ እንሳሮ ፊልም ተሸላሚ ሆኗል።

በምርጥ ሴት ተዋናይ ዘሪቱ ከበደ በወጣት በ97 ፊልም፣ ምርጥ ዋና ወንድ ተዋናይ ደግሞ ሄኖክ አሸናፊ ሱማሌው ቫንዳም ላይ ባሳዩት የትወና ብቃት ተሸላሚ መሆናቸው የ7ኛው ጉማ የፊልም ሽልማት ክስተቶች ነበሩ።

ከዚህም በተጨማሪም የባለፈው ዓመት የጉማ የሽልማት ዘርፍ የሕይወት ዘመን ተሸላሚ የሆኑት አንጋፋው ፀሐፌ ተውኔት ገጣሚና የዜማ ደራሲ እንዲሁም የፊልም ተዋናይ ተስፋዬ አበበ (ፋዘር) ነበሩ።

ተደጋጋሚ ወቀሳ የሚሰነዘርበት የኢትዮጵያ የፊልም ኢንዱስትሪ እንዲህ አይነት የማነቃቂያ ሽልማቶች ያስፈልጉታል። የፊልም ኢንዱስትሪውም ወቀሳው ብዙ ስለተደጋገመ እንጂ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታዩ ተወዳጅ ፊልሞችም ተፈጥረዋል።

በተለይም ባለፉት 20 ዓመታት የጎሉ እንቅስቃሴዎች ታይተውበታል። ለምሳሌ፤ በጀርመን ታዋቂ በሆነው ዓለም አቀፍ የፊልም ውድድር በርሊና መድረክ እና በዩናይትድ ስቴትሱ የሰንዳንስ ፊልም ፌስቲቫል ላይ ሽልማትን ያገኘው የኢትዮጵያው «ድፍረት» የተባለው ፊልም ተጠቃሽ ነው።

በፊልም ስራ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቱን በአሜሪካ ያጠናቀቀውና በርካታ ፊልሞችን እንደሰራ የሚነገርለት የጉማ ፊልም ሽልማት ዋና አዘጋጅ አቶ ዮናስ ብርሃነ መዋ፤ የጉማ ፊልም ሽልማት የተጀመረ ዓመት ለዶቼቬለ እንደተናገረው፤ ዝግጅቱ የፊልም ጥበብንና ጥበበኞችን ለመደገፍ የታሰበ ስነ ስርዓት ነበር። እነሆ አሁን እዚህ ደረጃ ላይ ደርሶ ብዙ መነቃቃትን ፈጠረ፣ ፊልሞችም በጥራት መሰራት ጀመሩ።

በጉማ የፊልም ሽልማት ሥነ ስርአት ላይ በተለያዩ ዘርፎች ከሚሰጠው ሽልማት በተጨማሪ ደግሞ፤ ለውድድር የማይቀርብ ዘርፍ አለ፤ ይህ ዘርፍ ‹‹የሕይወት ዘመን ተሸላሚ›› ነው። የሕይወት ዘመን ተሸላሚ የሚሆነውን ሰው መርጦ ማውጣት ነው ።

የመጀመሪያው የጉማ ፊልም ሽልማት ላይ የሕይወት ዘመን ተሸላሚ የነበሩት፤ ከአርባ ዓመት በላይ በፊልም ጥበብ ስራ ላይ የቆዩትና የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፊልም ዳሬክተር ሚሼል ፓፓታኪስ ናቸው።

ሚሼል ፓፓታኪስ፤ አባታቸው አዲስ አበባ ውስጥ የፊልም ቤት የከፈቱ የግሪክ ዜጋ ሲሆኑ እናታቸው ደግሞ ኢትዮጵያዊትና ትውልዳቸውም ኢትዮጵያ ውስጥ ነው።

የፊልም ሽልማት ስነ ስርዓቱን ‹‹ጉማ›› ሲል መጠሪያ የሰጠው የስነ ስርዓቱ ዋና አዘጋጅ እና የፊልም ስራ ባለሙያው ዮናስ ብርሃነ መዋ በወቅቱ ለዶቼቬለ እንደገለጸው፤ በሚሼል ፓፓታኪስ የተሰራው ጉማ ፊልም፤ ስያሜውን ከኦሮምኛ ቋንቋ እንደወሰደና፤ ካሳ ማለት እንደሆነ ተናግሯል።

ፊልሙ በኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥ ስላለው የግጭት አፈታት ባህል ላይ የሚያውጠነጥን ዘጋቢ ፊልም ነው። በአሁኑ ወቅት ፊልሙ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም ወመዘክር ውስጥ ይገኛል።

ጉማ የፊልም ሽልማት ስነ ስርዓት አሁን አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት እየታየ ላለው የቪዲዮ ፊልሞች ምርት መሰረት የጣሉትን ሰዎች ያስታወሰ፤ በዳኝነትም ሆነ አንጋፋ የፊልም ተዋናዮችን ታሳቢ ያደረገ መድረክ ነው።

የፊልም ኢንዱስትሪው እንዲያድግና፤ በኢኮኖሚው ውጤታማ እንዲሆን ሁሉም የተቻለውን ጥረት እንዲያደርግ ያነሳሳል። ሆኖም ግን የመንግሥትም ድጋፍ መደረግ አለበት። ምክንያቱም ፊልሞች የኢትዮጵያን ባህል በማስተዋወቁም ረገድ ሆነ ዓመታዊ ገቢን ከፍ እንዲል በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል።

በኢትዮጵያ የፊልም ስራ ዕድገት፣ ጥራትና ኢትዮጵያዊ ደረጃን የጠበቀ እንዲሆን የፊልም ሰራተኛ ማህበሩ ጥረት እያደረገ መሆኑንም የዘርፉ ሰዎች ሲናገሩ ቆይተዋል። ስለዚህ እንዲህ አይነት ሽልማቶች፤ መንግሥትንም፣ የፊልም ባለሙያውንም፣ የፊልም ተመልካቹንም መነቃቃት ይፈጥሩለታል ማለት ነው።

የፊልም ተመልካቹ ላይ ግን አንድ ትዝብት እናጋራ። ሁልጊዜ የፊልም ኢንዱስትሪውን መውቀስ ብቻውን ለውጥ አያመጣም። የኪነ ጥበብ ዘርፍ እና ስፖርት አንፃራዊ ነፃነት ስላለው ይመስላል ሰዳቢው ብዙ ነው። ከማድነቅ ይልቅ መተቸቱ የሚቀል ይመስላል። እርግጥ ነው ወቀሳ ስለበዛበት ነው ያላደገው ማለት አይቻልም፤ ቢሆንም ግን ጥሩ የተሰሩ ፊልሞችን ማድነቅና እውቅና መስጠት ደግሞ የበለጠ ያበረታታል። ስለዚህ እንደ ጉማ አይነት የፊልም ሽልማቶች ሲደረጉ ከፊልም ባለሙያው በተጨማሪ ተመልካቹም ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል።

ለምሳሌ፤ ያለፈውን ዓመት የጉማ ፊልም ሽልማት አስተያየቶች እናስታውስ። በመድረኩ በተለያየ ዘርፍ ከተሸለሙ ፊልሞች ይልቅ አጀንዳ ሆኖ የነበረው የሴት አርቲስቶች አለባበስ ነበር። የተሸለሙትን ፊልሞች የይዘትም ሆነ የቴክኒክ ጥራት ከመገምገም ይልቅ የአንድ ሴት አርቲስት አለባበስ የሳምንት አጀንዳ ሆኖ ነበር። እንዲያውም አሸናፊ የሆኑ ፊልሞች እስከሚረሱ ድረስ ዋናው መከራከሪያ አለባበስ ሆኖ ነበር። የዕለቱ የመድረክ አለባበስ ለዚያ ቅጽበት እንጂ በተሸለሙበት ፊልም ላይ የሚጨምረውም ሆነ የሚቀንሰው ነገር አልነበረም።

ይህ ሲባል ግን ከአዘጋጆችና ከተሸላሚዎችም ችግር የለም ማለት አይደለም። ከኢትዮጵያ ወግና ባህል ያፈነገጠ ነገር ማሳየትም ነውር ነው። ልክ በፊልሞቻቸው የኢትዮጵያን ወግና ባህል አሳይተው፣ ተደንቀው እንደተሸለሙት ሁሉ በመድረክ ላይም በእውናዊው ሕይወታቸውን ማሳየት አለባቸው።

የአገር ባህል ቀሚስ ለብሳ በተወነችው ፊልም ስትሸለም ራቁቷን ከመጣች፤ የፊልሙን ይዘት አታምንበትም ማለት ነው። ምንም እንኳን የገጸ ባህሪዋን ሕይወት ትኑር ባይባልም የአገርን ባህልና ወግ የሚጥስ ነገር ማሳየት ግን ነውር ነው፡ አዘጋጆችም ይህን ከግምት ማስገባት አለባቸው።

በአጠቃላይ የአገራችን የፊልም ኢንዱስትሪ የሚያድገው በኪነ ጥበብ ባለሙያውም፣ በታዳሚውም በመንግሥትም የጋራ ፍላጎት ነውና ከሁላችንም የሚጠበቀውን እናድርግ!

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## አካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚና ተሳታፊ ለማድረግ ያለመው የሕግ ማዕቀፍ

**ሰላማዊት ውቤ**

ኢትዮጵያ ውስጥ በአካል ጉዳተኞች ዙርያ በጣም በርካታ ሕጎች፣ ደንቦችና መመርያዎች አሉ። እነዚህን ህጎች መሬት አውርዶ ተግባራዊ ማድረግ ላይ ግን ችግሮች ነበሩ። በዚህ ምክንያት 20 ሚሊዮን የሚጠጉ አካል ጉዳተኞች በልማት ሥራዎች የሚፈለገውን ያህል ተጠቃሚ መሆን ሳይችሉ መቆየታቸውን ከሴቶችና ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል።

በሚኒስቴር መሥርያ ቤቱ የአካል ጉዳተኞች ዳይሬክቶሬት የአድቮኬሲና ኮሚኒኬሽን ቡድን መሪ አቶ ሲሳይ ጥላሁን እንደሚሉት ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በተለይም ሚኒስቴር መሥርያ ቤቱ በአዲስ መልክ ከተዋቀረ ወዲህ አካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚና ተሳታፊ ለማድረግ የሚያስችሉ ሕጎችና መመሪያዎች እየተዘጋጁ ይገኛሉ። ከዚህም መካከል የተጠቃለለ የአካል ጉዳተኞች የሕግ ማዕቀፍና የኢትዮጵያ ጀግኖች የጦር ጉዳተኞች ተኃድሶና ስልጠና ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ ዋንኛው ነው።

ማቋቋሚያ አዋጁ በኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛሉ ተብሎ የሚገመቱትን ከ17 እስከ 20 ሚሊዮን የሚደርሱ አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ያደርጋል ተብሎም ይታሰባል። ሶማሌ፣ ጋምቤላና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ላይም አዲስ አደረጃጀት በዳይሬክቶሬት ደረጃ ተዋቅሮ የተለያዩ ሥራዎችን እየሰራም ይገኛል ።

ቀደም ሲል ስራው በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካይነት ከሌላ ስራ ጋር ተዳብሎ በባለሙያ ብቻ ሲሰራበት መቆየቱንም አስታውሰው በአዲስ መልክ የተዋቀረው አደረጃጀትና የተዘጋጀው የሕግ ማዕቀፉ የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ ራሱን ችሎ በመሰራት የበለጠ ትኩረት እንዲያገኝ የሚያስችል መሆኑንም ገልጸዋል።



አቶ ሲሳይ ጥላሁን

ከዚህ ቀደም መስማት ለተሳናቸው ዜጎች የተሽከርካሪ መንጃ ፈቃድ አገልግሎት ይሰጥ የነበረበት አሰራር አልነበረም ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን መስማት የተሳናቸው ዜጎች የመንጃ ፈቃድ አገልግሎት እንዲያገኙ የማድረጉ ጉዳይ መተግበሩን ያወሳሉ።

‹‹እነዚህ መመሪያዎችም ሆኑ ሕጎች በብርቱ ወደ መሬት እንዲወርዱ ይፈለጋል ሕጎቹ በተጠቃለለ ሁኔታ የአካል ጉዳተኞችን ችግር ይፈታሉ ተብሎ ይታሰባል። የተጠቃለለ የአካል ጉዳተኞች የህግ ማዕቀፍ እየረቀቀ የሚገኘውም ይሄንኑ ዘርፈ ብዙ ፋይዳውን ታሳቢ በማድረግ ነው “ ብለዋል።

በተለይ ሕጎች ሲወጡ እዛም እዚህም በተበጣጠሰ ሁኔታ ይተገበሩ የነበሩትን ሰብሰብ አድርጎ ወደ አንድ ማምጣቱ ላይ ትልቅ አስተዋጾ እንደሚኖረው ገልጸው የሕግ ማዕቀፎቹን ወደ ተጠያቂነት በማምጣት ረገድ እንዲሁም የአካል ጉዳተኞችን ችግር እንዲፈቱ በማድረጉ ላይ ዓይነተኛ መሣርያ ይሆናል የሚል ዕምነት ተይዟል። የሕግ ማዕቀፉ የተለያዩ አገራት ተሞክሮ ተቀምሮ የተካተተበት በመሆኑ ዝግጅቱ ተጠናቅቆ በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ይበልጥ ውጤታማ እንደሚሆንም ይናገራሉ።

በማዕቀፉ ከተካተቱት የውጪ ተሞክሮ የሕግ ማዕቀፎች ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የአካል ጉዳተኞች ኮንቬንሽን ሕግ ለአብነት እንደሚጠቀስም አቶ ሲሳይ ጥላሁን ይናገራሉ። ሕጉ በ 2002 ዓ.ም ፀድቆ የሕግ አካል ለመሆን መብቃቱንም በማስታወስ ይሄንኑ ተሞክሮ በማዕቀፉ የተካተተውን ሕግ በርካታ የዓለም አገራት እንደፈረሙትና እየተገበሩት እንደሚገኙም አውስተዋል። በዚሁ ዙርያም አገራችን በየአራት ዓመቱ ለተባበሩት መንግስታት ሪፖርት የምታቀርብበት የሥራ ግንኙነት ሂደት እንዳለም ነው አቶ ሲሳይ የተናገሩት።

ከዚሁ የአካል ጉዳተኞች የሕግ ማዕቀፍ ዝግጅት ጎን ለጎንም የኢትዮጵያ ጀግኖች የጦር ጉዳተኞች ተሀድሶና ስልጠና ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ እየተዘጋጀ መሆኑንም ገልፀው ይሄም ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅቱ ተጠናቅቆ ወደ ተግባር በሚገባበት ወቅት ተበታትነው የሚገኙ በርካታ የጦር ጉዳተኞችን በማህበራዊው፣ በኢኮኖሚውና በፖለቲካዊው ልማት መስኮች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንደሚያደርግም አብራርተዋል።

እንደ አቶ ሲሳይ በተለይ የእንቅስቃሴ ችግር ላለባቸው የአካል ጉዳተኞች እንቅስቃሴያቸው እንዲፈታላቸው በማስቻሉ ረገድ የበዛ አበርክቶ ይኖረዋል። የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸውን የአካል ጉዳተኞች ችግር ይፈታ ዘንድም 41/2007 የሚል መመርያ ወጥቷል። የጦር አካል ጉዳተኞች ተንቀሳቅሰው መሥራት እንዲችሉ ድጋፍ የሚደረግበት ሁኔታ እንደሚመቻችም በመመርያው ተመላክቷል። ይሄም መመርያ አገራችን በፈረመችው የአካል ጉዳተኞች ኮንቬንሽን የሚደገፍበት ሁኔታ አለ። ባለፉት የለውጥ ዓመታት በዚህ ኢትዮጵያ በፈረመችው ኮንቬንሽን ብቻ 1 ሺህ 404 የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

‹‹እንደ አገር በመንግስት ደረጃ የሚታወቁና ዕውቅና ያገኙ በየጉዳት ዓይነታቸው የተደራጁ ስምንት የአካል ጉዳተኞ ማሕበራት አሉ ›› የሚሉት አቶ ሲሳይ በተጨማሪም የአካል ጉዳተኞች ዳይሬክቶሬት ጉዳተኞችን በየመስኩ ተጠቃሚና ተሳታፊ ከሚያደርጉ የሕግ ማዕቀፎችን ከማዘጋጀት በተጓዳኝ እነዚህኑ ጉዳተኞች የማብቃትና የመደገፍ ሥራዎችን እንደሚሰራም ገልጸዋል።

ከነዚህም መካከል በተደረገላቸው ድጋፍ በቅተው እስከ ክልል ወርደው በማዋቀር እየሰሩ የሚገኙት ዓይነ ስውራን ማሕበር፣ ማየትና መስማት የተሳናቸው ማሕበር፣ የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ማህበር፣ የሥጋ ደዌ ተጠቂዎች ማሕበር ይጠቀሳሉ። ከነዚህ በተጨማሪም 21 የአካል ጉዳተኞች ተሀድሶ በማድረግ ወደ ማሕበረሰቡ የሚቀላቀሉባቸው ማዕከላት እንዳሉም አክለዋል።

መንግስት ሥራቸውን ለመደገፍ በየዓመቱ ከፍተኛ በጀት እንደሚመድብም ይጠቁማሉ። ማሕበራቱ ከመንግስት በተጨማሪ በተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ የውጪ አገርና አገር በቀል ድርጅቶች እንደሚደገፉም ያወሳሉ። አቶ ሲሳይ ባለፉት ዓመታት ከዳይሬክቶሬቱ ጋር በመፈራረም ወደታች የወረደው ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ለአካል ጉዳተኞች መደረጉ መገለጫ መሆኑንም በማሳያነት ያቀርባሉ። የድጋፍ ፕሮጀክቶቹ በአካል ጉዳተኞች ማሕበራት ፌዴሬሽን እንደሚመጣና በዳይሬክቶሬቱ አማካኝነት የቁጥጥር፣ ክትትልና የድጋፍ ሥራ በመሥራት እስከ ታች የሚወርድበትና ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ እንዳለም ይገልፃሉ።

# ዓለም አቀፍ

## ዩክሬን የአዞቭስታል ተዋጊዎቿ ለሩሲያ ወታደሮች እጅ እንዲሰጡ ማዘዟን አረጋገጠች

አዲስ አበባ፣ ዩክሬን በአዞቭስታል የብረት ማምረቻ ፋብሪካ መሽገው ይዋጉ የነበሩ ወታደሮቿ ለሩሲያ ኃይሎች እጅ እንዲሰጡ ትዕዛዝ መስጠቷን ገለጸች።

የዩክሬን ጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ጽህፈት ቤት በማህበራዊ ትስስር ገጹ እንዳስታወቀው፥ በማሪዮፖል ግዛት በሚገኘው የአዞቭስታል የብረት ማምረቻ ፋብሪካ ውስጥ እንደመሸጉ በሩሲያ ጦር የተከበቡ የዩክሬን ወታደሮች እጅ እንዲሰጡ ትዕዛዝ ተሰጥቷቸዋል ብሏል።


በአዞቭስታል ብረት ፋብሪካ የተደረገው የመከላከል የውጊያ ዘመቻ መጠናቀቁን የገለጸው ጽ/ቤቱ ፥ የተከበቡ የዩክሬን ተዋጊዎችን ህይወት ለማትረፍ ለአካባቢው የአሀድ አዛዦች ትዕዛዝ ተላልፎ እንደነበርም ገልፀዋል።

በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሰረት የዩክሬን ወታደሮች ትናንት ለሩሲያ ጦር እጅ መስጠታቸውም ተዘግቧል።

እጅ የሰጡት 264 ወታደሮች ከአዞቭስታል ለቅቀው መውጣታቸውና 53 ከፉኛ የቆሰሉ ወታደሮች ሆስፒታል መግባታቸውም ተገልጿል።

የሩሲያ ምንጮች ደግሞ በአዞቭስታል ሰፊ ህንፃ ቅጥር ግቢ ውስጥ 2 ሺህ 200 የሚሆኑ ሰዎች ተከበው እንደሚገኙ ነው የገለጹት። ከእነዚህም መካከል ቢያንስ 600 የሚሆኑት ወታደሮች መሆናቸው ተጠቁሟል።

በዩክሬን ጦር ኃይሎች መግለጫ ፥ በአዞቭስታል የብረት ፋብሪካ ውስጥ የመሸጉ የዩክሬን ወታደሮች ጠላት ተጨማሪ ወታደራዊ ስራዎችን እንዳያከናውን ሲከላከሉ ቆይተዋል ነው ያለው። ትዕዛዝ የተሰጠውም ወታደሮቻችን ህይወታቸውን እንዲያተርፉ ነው ሲልም ነው የገለጸው።



በማሪዮፖል የሚገኘው የዩክሬን ወታደራዊ ኃይል ለ82 ቀናት የሩሲያን ጦር ሲወጋና አገሩን ሲከላከል ቀይቷል ሲልም መግለጫው ጦሩን አወድሷል።

የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቭሎዶሚር ዘለንስኪ በበኩላቸው፥ የዩክሬንን የመከላከያ ሰራዊታችን፣ የስለላ ድርጅታችን፣ እንዲሁም ተደራዳሪው ቡድን እና ዓለማቀፍ ተቋማት በሚያደርጉት የጋራ ስራ ታግዘን የወታደሮቻችንን ህይወት እንደምናተርፍ ተስፋ አደርጋለሁ ብለዋል።

ዩክሬን የጀግኖችን ህይወት ትጠብቃለች ያሉት ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ፥ ይህም የዩክሬን መንግስት እና ወታደራዊ ኃይሉ መርህ መሆኑን ተናግረዋል።

ወታደሮቻችን ወደ አገራቸው ለመመለስም ከሩሲያ ጋር የድርድር ሂደቱ የቀጠለ መሆኑን እና ሂደቱም ብዙ ስራዎችን እና ትዕግስትን የሚጠይቅ መሆኑን ዘለንስኪ አመላክተዋል።

የዩክሬን የመከላከያ ምክትል ሚኒስትር አና ማሊያር እና የዩክሬን ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም በጋራ እንደገለፁትም ተማርከው እጅ የሚሰጡ የዩክሬን ወታደሮች በሩሲያ የጦር እስረኞች ይለወጣሉ ብለዋል።

ይሁን እንጂ የልውውጡ ስምምነት ገና ያልተወሰነ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን ፥ ሞስኮ ስለ ልውውጥ ሂደቱ እስካሁን ምንም ዓይነት ይፋዊ መግለጫ እንዳልሰጠች ተመላክቷል።

የሩሲያ ጦር የዩክሬን ከፍተኛ የውጊያ ማዕከል የሆነውን የአዞቮስታል ምሽግ ከዩክሬን ወታደሮች ማስለቀቅ ከቻለ የወደብ ከተማዋንና የአገሪቱን ሁለተኛ ትልቋን መዲና ማሪዮፖልን በአጭር ጊዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንደሚቆጣጠር ያመላክታል ሲል አር ቲ ዘግቧል።

# ስፖርት





# ወርቃማ ተተኪዎች የነጠፉባት የሯጮች ምድር

ብርሃን ፈይሳ

ዓለም በልዩነት ከሚያውቃቸው የኢትዮጵያ ከተሞች መካከል አንዷ በቆጂ ናት። ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ስኬት የጀርባ አጥንት የሆኑ እንቁ አትሌቶች ከዚህች ትንሽ ከተማና አካባቢዋ ፈልቀው ዘመን የማይሽረው ታሪክ ሰርተዋል። ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ መድረክ ከሰበሰበቻቸው 58 ሜዳሊያዎች መካከል 18 የሚሆኑት ሜዳሊያዎች(10የወርቅ፣ 3 የብር እና 5 የነሃስ) ከዚህ ስፍራ በተገኙ አትሌቶች የተሰበሰቡ ናቸው። ይህ ቁጥር በቆጂን እንደ አንድ አገር ብናስባት ከአንድ ምዕተ ዓመት በላይ በዘለቀው የኦሊምፒክ ታሪክና አጠቃላይ የሜዳሊያ ሰንጠረዥ ከዓለም 59ኛ ደረጃ ላይ ያስቀምጣታል። በኦሊምፒክ መድረክ በተለያዩ አጋጣሚዎች የተሳትፎ ታሪክ ያላቸው ከስልሳ በላይ አገራት አንድም ሜዳሊያ ባላገኙበት ሁኔታ በቆጂ እንደ አንድ አገር ታሳቢ ብትደረግ እንደ ግብፅ፣ ሱዳን፣ ታንዛኒያ፣ ኢንዶኔዢያና ሌሎች በርካታ የዓለማችን ታላላቅ አገራት ያላገኙትን ደረጃና ክብር በማግኘቷ ዓለም ‹‹የሯጮች ምድር›› ብሎ ቢጠራት አይገርምም።

በቆጂ ተፈጥሮ ያደላት ለሩጫ ምቹ የሆነ የአየር ፀባይዋ ከመልካ ምድሯ አቀማመጥና የነዋሪዎቿም አትሌቲክስ ባህል የማድረግ ዝንባሌ ለኢትዮጵያ መልካም ገጽታ ግንባታ በረከት ሆኗል። ይሁንና ይህች የሯጮች ምድር ባለፉት ዘመናት እንዳበረከተቻቸው በርካታ ወርቃማ ኦሊምፒያን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ተተኪዎችን በማፍራት ረገድ መዳከም እያሳየች እንደምትገኝ መታዘብ ይቻላል። በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ኢትዮጵያ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከምታስመዘግበው ውጤት በመነሳትም በቆጂ እንዳላት እምቅ አቅምና ባለፉት ዘመናት እንዳፈራቻቸው ብርቅየ አትሌቶች አንፃር በመጣችበት ፍጥነት እየተጓዘች ነው ለማለት አያስደፍርም። ለስፖርቱ ቅርብ የሆኑና የአካባቢው ነዋሪዎችም ይህንን ቁጭት ይጋሩታል።



በቆጂ እንደ ቀድሞው ወርቃማ አሊምፒያንን ለማፍራት ትኩረት ሊሰጣት እንደሚገባ የስኬታማ አትሌቶች መልማይ አሰልጣኝ ስንታየሁ እሸቱ ተናግረዋል፣

በዚህ ወቅት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ከሆነችው አንጋፋዋ አትሌት ኮሎኔል ደራርቱ ቱሉ አንስቶ እንደ ቀነኒሳ በቀለ፣ ታሪኩ በቀለና ስኬታማው የዲባባ የአትሌቲክስ ቤተሰብ እንዲሁም እስከ አሁን ድረስ በርካታ ውጤታማ አትሌቶችን ከትምህርት ቤቶች በመመልመል ከሚታወቁ አሰልጣኞች መካከል አንዱ ስንታየሁ እሸቱ ናቸው። እኚህ አሰልጣኝ በአሁኑ ወቅት በበቆጂ የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል የረጅም ርቀት አሰልጣኝ በመሆንም እየሰሩ ይገኛሉ። የውጭ አገራት ዜጎች ጭምር ስራቸውን በዘጋቢ ፊልም በመቅረጽ ለዓለም ያሳዩላቸውና ለበርካታ አትሌቶች መሰረት የጣሉት አሰልጣኝ ስንታየሁ በሯጮቹ ምድር አሁን አሁን ወደ ስፖርቱ የሚሳቡ ታዳጊዎች ቁጥር እየቀነሰ መምጣቱን እንዳስተዋሉ አልሸሸጉም።

ቀደም ባለው ወቅት ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲያሰለጥኑላቸው አምጥተው እስከመስጠት ይደርሱ እንደነበር የሚያነሱት አሰልጣኙ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህ ዓይነቱ ሁኔታ እየቀነሰ መምጣቱን ነው የሚጠቁሙት። ለዚህ ደግሞ አንድም ከወቅቱ ጋር የተያያዘው ሁኔታ ተጽእኖ በማሳደሩ መሆኑን ይናገራሉ። ከዚህ ባሻገር አካባቢው ቀድሞ እንደነበረው እንጂ አበረታችና አትሌቶችን ሊያነሳሳ የሚችል ነገር አለመኖሩም ለዚህ ሚና እንዳለው ያስረዳሉ። በእርግጥ በማዕከሉ የሚሰለጥኑ ታዳጊዎች በየዓመቱ ከአትሌቲክስ ፌዴሬሽን የትጥቅ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። ነገር ግን እንደ አጠቃላይ ከተማዋ ውስጥ ያለው ሁኔታ አትሌቶችን ሊያበረታታ የሚችል አለመሆኑን አሰልጣኙ ይናገራሉ።

በቅርቡ የኢፌዴሪ ቱሪዝም ሚኒስቴር የጀመረው በቆጂን የአትሌቲክስ ስፖርት ማዕከል ማድረግ እንዲሁም በየዓመቱ በከተማዋ ውድድር ማካሄዱ ታዳጊዎችን የማነቃቃትና የመሳብ አንዱ መንገድ ሊሆን እንደሚችልም አሰልጣኝ ስንታየሁ ይጠቁማሉ። ከዚህ ጎን ለጎን በስፖርቱ ላይ የሚሰሩት መንግስታዊ አካላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በመወጣት ዳግም በቆጂን የኦሊምፒክ ሜዳሊያዎች መፍለቂያ ማድረግ እንደሚቻል ያስባሉ።

የበቆጂ ፍሬ የሆነችው አትሌት መሰረት ሂርጳ፤ በማሰልጠኛ ማዕከሉ አልፋ አሁን የቢሾፍቱ ከተማ አትሌቲክስ ክለብ አትሌት ለመሆን በቅታለች። አትሌቷ በቱሪዝም ሚኒስትርና ታላቁ ሩጫ በተዘጋጀው የ7ኪሎ ሜትር ሩጫ ተሳትፋ በአሸናፊነት ነበር ያጠናቀቀችው። ተወልዳ ባደገችበት በቆጂ ሌሎች አትሌቶችን በመመልከት ወደ ስፖርቱ ብትገባም አሁን ላለችበት ደረጃ ለመብቃት በርካታ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ማሳለፏን ታስታውሳለች። አትሌቶች በራሳቸው ጥረት ካልወጡ በቀር የትጥቅ እና የስልጠና ሁኔታ አለመመቻቸት እንዲሁም ድጋፍ ማጣት አሁንም ድረስ በቆጂ ወርቃማ ኦሊምፒያንን በብዛት እንዳታፈራ እንቅፋት መሆናቸውን ትናገራለች። በዚህም ምክንያት ከቀድሞ አንጻር የአትሌቶች ቁጥር መቀነስ እያሳየ ነው። በመሆኑም በሌሎች አገራት አትሌቶች የሚደረግላቸው ድጋፍ በቆጂ ላይም ቢደረግ ችሎታ ያላቸው ምርጥ አትሌቶችን በብዛት ማፍራት እንደሚቻልም እምነት አላት።

ወጣት ብሩክ ከድር የበቆጂ ከተማ ነዋሪ ሲሆን፤ በቆጂ እንደ ወርቃማ አትሌቶች ምንጭነቷ ትኩረት ያላገኘችና መሰረተ ልማትም ያልተሟላላት ከተማ መሆኗን ይገልጻል። የማሰልጠኛ ማዕከላትንና አካዳሚዎችን በመገንባት ስፖርቱን ማበረታታት ባለመቻሉ ስፖርቱ የመቀዛቀዝ አዝማሚያ እያሳየ እንደሚገኝም ያስቀምጣል። ይህን ሁኔታ በተለያየ ጊዜ ትኩረት እንዲያገኝ ለማድረግ ቢሞከርም በቆጂ እንደ አትሌቲክስ ምንጭነቷ መቀጠል ሳትችል ቀርታለች። ‹‹እንደ አገር በትልልቅ ውድድሮች ውጤት ለማጣት ምክንያት ከሚሆኑት መካከል አንዱ የበቆጂ አትሌቶችን አለማፍራት ነው›› የሚለው ወጣቱ፣ በቱሪዝም ሚኒስቴር የተጀመረውን ዓይነት በአካባቢው ስፖርቱን የማነቃቃት ስራ በማስፋትና ለስፍራው ይበልጥ ትኩረት በመስጠት መፍትሄ ማምጣት እንደሚቻል አስታውቋል፡፡

## ከገጽ 30 የዞረ



1. The Applicant shall submit only one application, either in its own name or as a member of a Joint Venture (JV). If an Applicant (including any JV member) submits or participates in more than one application, those applications shall be all rejected. However, the same Subconsultant may participate in several applications.

If the Applicant is a joint venture (JV), the expression of interest shall include:

•. A copy of the JV Agreement entered into by all members, or

•. A letter of intent to execute a JV Agreement, signed by all members together with a copy of the Agreement proposal,

In the absence of this document, the other members will be considered as Subconsultants.

2. A Consultant will be selected in accordance with the Quality Cost Based Selection (QCBS) method set out in the Consultant Guidelines.
3. The applicants shall bear all costs associated with the preparation and submission of the Application and ATA will not in any case be responsible and liable for the costs incurred.
4. Expressions of interest must be delivered to the address below at or before **2:00 PM June 02, 2022.** Electronic application will not be permitted. Late applications will be rejected. Applications will be opened in the presence of the bidders' representatives who choose to attend in person at the address below at **2:30 PM June 02, 2022,** Late Application will no longer be considered.
5. The Application must be submitted in the English language. All required information must be provided, responding clearly and concisely to all the points set out. Any application which does not fully and comprehensively address this Request for Expression of Interest may be rejected.

ATA reserves the right to accept or reject any Application, and to cancel the procurement process and reject all Applications, at any time without thereby incurring any liability to the affected applicants or any obligation to inform the affected applicants of the ground for ATA's action.

The Application must be submitted either by hand to ATA tender box with office address given below.

**Ethiopian Agricultural Transformation Agency (ATA)**
**Senior Operation Director Office, 4th floor**
**Bole, off Meskel Flower Road /Behind Mega Building – Across Commercial Graduates Association, Streeling Building 74th floor**
**Tel. +251-115 -570678/85 or cell phone +251911-646029**
**Fax + 251-115 570668**
**Addis Ababa, Ethiopia**

**Interested Applicants may obtain further information at the address: Yohannes.tadesse@ata.gov.et or at the address mentioned above prior to May 25, 2022, during office hours 2:30Am-5:30Pm**

**Ethiopian Agricultural Transformation Agency**